# የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት

## ማዕከላዊ ነጋሪት ጋዜጣ

## MAEKELAWI NEGARIT GAZETA

## OF THE CENTRAL ETHIOPIA REGIONAL STATE

ሆሳዕና 2ኛ ዓመት ቁጥር

የካቲት 20 ቀን 2'*፲6 ዓ.ም

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት

ጠባቂነት የወጣ

Hossana 2nd Year No

28 February /2024


## አዋጅ ቁጥር 10/2016 ዓ.ም

## የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ገቢ ግብር አዋጅ

### መግቢያ

የክልላችን የኢኮኖሚ ዕድገት ከደረሰበት ደረጃ ጋር የተጣጣመነ እና የኢኮኖሚውን ዕድገት የሚያግዝ ዘመናዊና ቀልጣፋ የግብር ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

የግብር አከፋፈል ሥርዓቱ ፍትሀዊነት ያለውና የተሟላ እንዲሆን ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በሥራ ላይ ያለውን የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 165/2009ን ከክልሉ ህገ-መንግስት ጋር የተጣጣመ እንዲሆን በአዲስ አዋጅ መተካት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሕገ-መንግስት አንቀፅ ፶፭ ንዑስ አንቀፅ 3 መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## Proclamation No10./2024

## Central Ethiopia Regional State Income Tax Proclamation

### Preamble

**WHERAS**, it has become necessary to introduce modern and efficient tax system that supports the economic development of our region, and which is in accord with the level of economic development achieved so far;

**WHERAS**, it is found essential to make the tax system fair and complete;

**WHERAS** it is necessary to replace the current Income Tax Proclamation No. 165/2005 with a new Proclamation to be consistent with the Region constitution;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with sub-article 3 of Article 55 of the Constitution of the Central Ethiopia Region State, it is hereby proclaimed as follows:

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ “የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር10/2016 ዓ.ም” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጉም**

በዚህ አዋጅ የተለየ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር በታክስ አስተዳደር አዋጁ ትርጉም የተሰጠው ቃል ወይም ሐረግ በዚህ አዋጅ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለ እንደሆነ በታክስ አስተዳደር አዋጁ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም፡-

1. "የገንዘብ መጠን” ማለት በዓይነት የተገለፀ መጠንንም ይጨምራል፡፡
2. "የንግድ ሥራ” ማለት፣
   ሀ/ በተከታታይ ወይም ለአጭር ጊዜ ለትርፍ የሚከናወን ማንኛውም የኢንዱስትሪ፣ የንግድ፣ የሙያ ወይም ቮኬሽናል ሥራ ሲሆን ተቀጣሪ ለቀጣሪው የሚሰጠውን አገልግሎት ወይም ቤት ማከራየትን አይጨምርም፣
   ለ/ በንግድ ሕግ መሠረት የንግድ ሥራ ነው ተብሎ እውቅና የተሰጠው ሌላ ማንኛውም ሥራ፣ ወይም
   ሐ/ ሕንጻ ማከራየትን ሳይጨምር የኩባንያው ዓላማ ምንም ቢሆን ማንኛውም የአክሲዮን ማህበር ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር

## PART ONE

## GENERAL

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as the “Central Ethiopia Region State Income Tax Proclamation No. 10/2024.’’

2. **Definition**

A term used in this Proclamation that is defined in the Tax Administration Proclamation shall have the meaning in the Tax Administration Proclamation. In addition, unless defined otherwise in this Proclamation:-

1. “Amount” include an amount-in-kind;
2. “Business” means
   a) any industrial, commercial, professional, or vocational activity conducted for profit and whether conducted constantly or short-term, but does not include the rendering of services as an employee or the rental of buildings;
   b) any other activity recognised as a trade under the Commercial Code; or
   c) any activity, other than the rental of buildings, of a share company or private limited company whatever the objects of the company;

| | |
|---|---|
| የሚሠራው ማንኛውም ሥራ፡፡ | |
| 3. "የንግድ ሥራ ሀብት" ማለት የንግድ ሥራ በማከናወን ሂደት በሙሉ ወይም በከፊል የንግድ ሥራ ገቢ ለማግኘት የተያዘ ወይም ጥቅም ላይ የዋለ የንግድ ሥራ ሀብት ነው፡ : | 3. "Business asset" means an asset held or used in the conduct of a business wholly or partly to derive business income; |
| 4. "የንግድ ሥራ ገቢ" በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፳፩ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፡፡ | 4. "Business income" shall have the meaning in Article 21 of this Proclamation; |
| 5. "ማግኘት" ማለት፣ | 5. "Derive" means: |
| ሀ/ ለንግድ ሥራ እና ለኪራይ ገቢ ግብር፤ | a) for the business and rental income tax: |
| ፩. በተሰብሳቢና ተከፋይ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ ሂሳቡን ለሚይዝ ግብር ከፋይ፣ ለመቀበል የሚያስችል መብት ማግኘት፣ | (1) for a tax payer accounting for tax on an accruals basis, the arising of the right to receive; or |
| ፪. ሂሳቡን በጥሬ ገንዘብ እንቅስቃሴ ላይ በተመሠረተ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ ለሚይዝ ግብር ከፋይ፣ መቀበል፣ ወይም | (2) for a taxpayer accounting for tax on a cash basis, received; or |
| ለ/ በዚህ አዋጅ መሠረት ለተጣለ ማንኛውም ሌላ ግብር መቀበል ነው፡፡ | b) for any other tax imposed under this Proclamation, received; |
| 6. **"የትርፍ ድርሻ"** ማለት አንድ ድርጅት ለአባላቱ የሚያከፋፍለው ትርፍ ሲሆን የሚከተሉትን ይጨምራል፡፡ | 6. "Dividend" means a distribution of profits by a body to members and includes the following: |
| ሀ/ የድርጅቱ ካፒታል በከፊል ሲቀንስ ለአባሉ በአባልነቱ ተመላሽ የሚደረግለት ከካፒታሉ ውስጥ ከተቀነሰው በስሙ ከተመዘገበ የአባልነት ጥቅም ዋጋ በላይ የሆነው የገንዘብ መጠን፤ | a) an amount returned by a body to a member in respect of a membership interest on a partial reduction in the capital of the body to the extent that the amount returned exceeds the amount by which the nominal value of the membership interest was reduced; |

| | |
|---|---|
| ለ/ ድርጅቱ መልሶ በመሸጡ ወይም በመዘጋቱ ወይም ኩባንያው በመፍረሱ ወይም ሽርክና በመቋረጡ ምክንያት የአባልነት ጥቅም ሲሰረዝ ለአባሉ ተመላሽ የተደረገለት በካፒታሉ ውስጥ ከነበረው በስሙ ከተመዘገበ የአባልነት ጥቅም ዋጋ በላይ የሆነው የገንዘብ መጠን፤ | b) an amount returned by a body to a member on redemption or cancellation of a membership interest, including on retailing or interdict or liquidation of a company or termination of a partnership, to the extent that the amount returned exceeds the nominal value of the membership interest; |
| ሐ/ ድርጅቱ ለአንድ የድርጅት አባል ወይም ከአባሉ ጋር ግንኙነት ላለው ሰው ትርፍ የማከፋፈል ውጤት በሚያስከትል ግብይት ያበደረው ማንኛውም የገንዘብ መጠን፣ ለአንድ ሀብት ወይም አገልግሎት የፈጸመው ክፍያ፣ የማንኛውም ሀብት ወይም የቀረበ አገልግሎት ዋጋ ወይም የተተወ የብድር ዕዳ፤ | c) the amount of any loan, payment for an asset or services, value of any asset or services provided, or any debt obligation released by a body to, or in favour of, a member or a related person of a member to the extent that the transaction is, in substance, a distribution of profits; |
| 7. "ተቀጣሪ" ማለት ራሱን ችሎ የሚሠራን የሥራ ተቋራጭ ሳይጨምር በሌላ ሰው መሪነትና ቁጥጥር ሥር ሆኖ አገልግሎት ለመስጠት በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት የተቀጠረ ግለሰብ ሲሆን የድርጅት ዳይሬክተርን ወይም በድርጅቱ አመራር ውስጥ ኃላፊነት የተሰጠውን ሌላ ሰው እንዲሁም ተሿሚንና የሕዝብ ተመራጭን ጨምሮ የመንግሥት ሥራ ኃላፊን ያጠቃልላል፡፡ | 7. "Employee" means an individual engaged, whether on a permanent or temporary basis, to perform services under the direction and control of another person, other than as an independent contractor, and includes a director or other holder of an office in the management of a body, and government appointees and elected persons holding public offices; |
| 8. "ቀጣሪ" ማለት ተቀጣሪን የቀጠረ ወይም ለተቀጣሪው ደመወዝ የሚከፍል ሰው ነው፡፡ | 8. "Employer" means a person who engages or remunerates an employee; |

9. "ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ" በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፪ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል።

፲. "ከግብር ነፃ የሆነ ገቢ" ማለት በዚህ አዋጅ ሠንጠረዥ "ሠ" መሠረት ከግብር ነፃ የሆነ ገቢ ነው።

01. "የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች" ማለት በፌዴራል የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ አዋጅ ቁ.647/2006 የተደነገጉት የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች ናቸው።

02. "ጠቅላላ ገቢ" ማለት ወጪዎች ተቀናሽ ከመደረጋቸው በፊት አንድ ሰው ያገኘው በሠንጠረዥ "ለ" እና "ሐ" ሥር የሚወድቅ ጠቅላላ ገቢ ነው።

03. "የማይንቀሳቀስ ንብረት" በአንቀጽ ፴፮ በተደነገገው መሠረት በማዕድን ሀብት ላይ ያለን መብት ወይም የማዕድን መረጃን ይጨምራል።

04. "ገቢ" ማለት መደበኛ ያልሆነ ገቢን ጨምሮ ከማንኛውም ምንጭ በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት የተገኘ ወይም በማንኛውም መንገድ ለግብር ከፋዩ የተከፈለው፣በስሙ የተያዘለት ወይም የተቀበለው ማንኛውም የኢኮኖሚ ጥቅም ነው።

05. "ራሱን የቻለ ሥራ ተቋራጭ" ማለት ሥራውን በአመዛኙ በራሱ የመምራትና የመቆጣጠር በቂ ሥልጣን በሚሰጠው ውል መሠረት አገልግሎት የሚሰጥ ግለሰብ ነው።

9. "Employment income" shall have the meaning in Article 12 of this Proclamation;

10. "Exempt income" means income exempt from tax under Schedule 'E' of this Proclamation;

11. "Financial reporting standards" means the financial reporting standards stipulated under the Federal Financial Report Preparation and Presentation Proclamation no.647/2014;

12. "Gross income", in relation to a person, means the total income taxable under Schedules 'B' or 'C' derived by a person without deduction of expenditures;

13. "Immovable property" includes a mineral resource right, or a mineral information, as defined in Article 36 of this Proclamation;

14. "Income" means every form of economic benefit, including non-recurring gains, in cash or kind from whatever source derived and in whatever form paid to a tax payer;

15. "Independent contractor" means an individual engaged to perform services under an agreement by which the individual retains substantial authority to direct and control the manner in which the services are to be performed;

| | |
|---|---|
| ፩6. "ወለድ" ማለት ገንዘብን ለመጠቀም ወይም የክፍያ ጊዜን ለማራዘም በየጊዜው ወይም በአንድ ጊዜ የሚከፈል የገንዘብ መጠን ሲሆን ቅናሽን፣ ፕሪሚየምን ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ክፍያዎችንም ይጨምራል፡፡ | 16. "Interest" means a periodic or lump sum amount, however described as consideration for the use of money or being given time to pay, and includes a discount, premium, or other functionally equivalent amount; |
| ፩7. "የሥራ አመራር ክፍያ" ማለት ለሥራ አመራር ወይም አስተዳደራዊ አገልግሎት የሚከፈል የገንዘብ መጠን ሲሆን ከመቀጠር የሚገኝ ገቢን አይጨምርም፡፡ | 17. "Management fee" means an amount as consideration for the rendering of any managerial or administrative service, but does not include employment income; |
| ፩8. "ኃላፊ" ማለት የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ገቢዎች ቢሮ ኃላፊ እና እንደአግባብነቱ በየአስተዳደር እርከኑ የሚገኙ መምሪያዎች፣ ጽ/ቤቶች እና የታክስ ማዕከላትን ሃላፊዎችን ነው፡፡ | 18. "Head" means the Head of Central Ethiopia Region Revenue Bureau and the heads of departments, offices and tax centers at each administrative level respectively; |
| ፩9. "ቢሮ" ማለት የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ገቢዎች ቢሮ እና እንደአግባብነቱ በየአስተዳደር እርከኑ የሚገኙ መምሪያዎች፤ ጽ/ቤቶች እና የታክስ ማዕከላትን ይጨምራል፡፡ | 19. "Bureau" means Central Ethiopia Region Revenue Bureau and includes the relevant departments, offices, and tax centers at each level of administration. |
| ፳ "መቀበል" የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡፡ | 20. "Received", includes: |
| ሀ/ ግብር ከፋዩ በሚያቀርበው ጥያቄ ወይም በሕግ መሠረት ገንዘቡ በግብር ከፋዩ ስም ጥቅም ላይ ሲውል፣ | a) applied on behalf of the Taxpayer either at the request of the Taxpayer or under any law; |
| ለ/ ለግብር ከፋዩ ጥቅም ተብሎ ገንዘቡ መልሶ ሥራ ላይ ሲውል ወይም ሲጠራቀም ወይም ደግሞ ለካፒታል ማሳደጊያ ሲውል፣ | b) reinvested, accumulated, or capitalised for the benefit of the Tax Payer; |
| ሐ/ ለግብር ከፋዩ ጥቅም ወደ ባንክ ሂሳብ ውስጥ ሲገባ ወይም ወደ | c) credited to an account or carried to a reserve for the benefit of the Taxpayer; or |

መጠባበቂያ ገንዘብ ሲዘዋወር ፣

መ/ በሌላ በማናቸውም መልኩ ለግብር ከፋዩ የተያዘለት ሲሆን፣

፳፩ "ሮያሊቲ" ማለት ከዚህ በታች ከተመለከቱት ለማንኛውም ጉዳይ በአንድ ጊዜ ወይም በየጊዜው የሚከፈል የገንዘብ መጠን ነው፡፡

ሀ/ ማንኛውንም የሥነ-ጽሑፍ፣ የሥነ-ጥበብ፣ ወይም የሳይንሳዊ ሥራ የቅጂ መብት ሲሆን፣ የሲኒማቶግራፊ ፊልሞችና ለሬድዮ፣ ለቴሌቪዥን ወይም ለኢንተርኔት ሥርጭት የሚውሉ ፊልሞችና ቴፖችን መጠቀም ወይም ለመጠቀም መብት ማግኘትን ይጨምራል፤

ለ/ ከቴሌቪዥን ወይም ከሬድዮ ወይም ከኢንተርኔት ሥርጭት ጋር ተያይዞ በሳተላይት፣ በኬብል፣ በኦፕቲክ ፋይበር፣ ወይም በሌላ ተመሳሳይ ቴክኖሎጂ የሚተላለፉ ወይም የሚታዩ ምስሎችን፣ ወይም ድምፆችን ወይም ሁለቱንም መቀበል ወይም ለመቀበል የሚያስችል መብት ማግኘት፤

ሐ/ ማንኛውንም የፈጠራ ባለቤትነት መብት፣ ፈጠራ፣ የንግድ ምልክት፣ ንድፍ ወይም ሞዴል፣ ፕላን፣ የሚስጥር ቀመር ወይም ሂደት ወይም ሌላ ተመሳሳይ ንብረት ወይም መብት መጠቀም ወይም የመጠቀም መብት ማግኘት፤

መ/ ማንኛውንም ኢንዱስትሪያዊ፣ የንግድ ወይም ሳይንሳዊ መሣሪያ መጠቀም ወይም ለመጠቀም መብት ማግኘት፤

d) otherwise made available to the Taxpayer;

21. “Royalty” means a periodic or lump sum amount to be paid as consideration for any of the following:

a) the use of, or the right to use any copyright of literary, artistic, or scientific work, including cinematography films, and films and tapes for radio, television, or internet broadcasting;

b) the receipt of, or right to receive, visual images or sounds, or both, transmitted by satellite, cable, optic fiber, or similar technology in connection with television, radio, or internet broadcasting;

c) the use of, or the right to use any patent, invention, trademark, design or model, plan, secret formula or process, or other like property or right;

d) the use of, or the right to use any industrial, commercial, or scientific equipment;

ሠ/ ማንኛውንም ኢንዱስትሪያዊ፣ የንግድ ወይም ሳይንሳዊ ተሞክሮ የሚመለከት መረጃ መጠቀም ወይም የመጠቀም መብት ማግኘት፤

ረ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከፊደል ተራ (ሀ-ሠ) የተዘረዘሩትን ንብረቶች ወይም መብቶች መጠቀም እንዲቻል በተጨማሪነትና በተቀጽላነት የሚሰጥ ድጋፍ፤

፳፪ "የግብር ዓመት" ማለት

ሀ/ ለግለሰብ ሲሆን፣ ቢሮው በጽሑፍ ማስታወቂያ ፈቃድ ካልሰጠ እና በጽሑፍ ማስታወቂያው የተወሰኑትን ቅድመ-ሁኔታዎች በማሟላት ግለሰቡ የራሱን የሂሳብ ዓመት ካልተጠቀመ በስተቀር፣ ከሐምሌ ፩ ቀን እስከ ሰኔ ፴ ቀን ያለው የአንድ ዓመት ጊዜ ነው፡፡

ለ/ ለድርጅት ሲሆን የድርጅቱ የሂሳብ ዓመት፤ ወይም

ሐ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፰ የተወሰነው የመሸጋገሪያ የሂሳብ ዓመት ነው፡፡

፳፫ "ግብር ከፋይ" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት ግብር የመክፈል ግዴታ የተጣለበት ሰው ነው፡፡

፳፬ "የቴክኒክ ክፍያ" ማለት ለቴክኒካዊ፣ ሙያዊ፣ ወይም ለማማከር አገልግሎት የሚከፈል ክፍያ ሲሆን፣ የቴክኒክ ወይም ሌሎች ባለሙያዎችን ለመጠቀም የሚከፈል ክፍያን ይጨምራል፡፡

፳፭ "የንግድ ዕቃ" የሚከተሉትንም ይጨምራል፡፡

e) the use of, or the right to use any information concerning industrial, commercial, or scientific experience;

f) the supply of assistance that is ancillary and subsidiary to, and is furnished as a means of enabling the application or enjoyment of property or a right referred to in paragraphs (a) - (e) of this sub-article;

22. "Tax year" means:

a) for an individual, the one-year period from 1st Hamle to 30th Sene, unless the Bureau has granted permission, by notice in writing and subject to such conditions as may be specified in the notice, for the individual to use its accounting year as the individual's tax year;

b) for an organization, the accounting year of the organization; or

c) a transitional accounting year as determined under Article 28 of this Proclamation;

23. "Taxpayer" means a person liable for tax under this Proclamation;

24. "Technical fee" means a fee for technical, professional, or consultancy services, including a fee for the provision of services of technical or other personnel;

25. "Trading stock" includes:

ሀ/ ማንኛውም የተመረተ፣ የተፈበረከ፣ የተገዛ ወይም ለማምረት፣ ለመሸጥ ወይም ለመለወጥ በማናቸውም ሁኔታ የተገኘ ዕቃ፤

ለ/ በማምረት ወይም በመፈብረክ ሂደት ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውል ማንኛውም ጥሬ ዕቃ ወይም አላቂ ዕቃ፣ ወይም

ሐ/ ለጭነት ወይም ለሥራ የሚያገለግሉ እንስሳትን ሳይጨምር ማንኛውም እንስሳ፤

፳፮ "ግብር ቀንሶ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት የተጣለበት ሰው" ማለት ከሚከፍለው ክፍያ ላይ በዚህ አዋጅ ክፍል አስር መሠረት ግብር ቀንሶ የማስቀረት ኃላፊነት ያለበት ሰው ሲሆን፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፹፱ መሠረት ከሚያገኘው ክፍያ ላይ ግብር ራሱ ቀንሶ የማስቀረት ኃላፊነት ያለበትንም ሰው ይጨምራል፡፡

፳፯ "ግብር ተቀናሽ የሚደረግበት ገቢ" ማለት በዚህ አዋጅ ክፍል አሥር መሠረት ግብር ተቀንሶ የሚያዝበት ገቢ ማለት ነው፡፡

፳፰ “ድርጅት” ማለት ኩባንያ፤ የሽርክና ማህበር፣ የመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም የመንግሥት የፋይናንስ ድርጅት ወይም ሌላ በኢትዮጵያ ወይም በውጭ ሀገር የተመሠረተ ድርጅት ነው፡፡

፳፱ “ሰው” ማለት ግለሰብ፣ ድርጅት፣

a) anything produced, manufactured, purchased, or otherwise acquired for manufacture, sale, or exchange;

b) any raw materials or consumable used in a production or manufacturing process; or

c) livestock, but not including animals used as beasts of burden or working beasts;

26. “Withholding agent” means a person liable to withhold tax under Part Ten of this Proclamation from a payment made by the person and includes a person required to self-withhold tax under Article 89of this Proclamation from an amount received by the person;

27. “Withholding income” means income from which tax is required to be withheld under Part Ten of this Proclamation;

28. “Organization” means a company, a share company, developmental organization of a government or financial organization of a government or other organization established in Ethiopia or in abroad; and

29. “Person” means an individual; an organization; a government or sub political

መንግሥት ወይም የአንድ መንግሥት ንዑስ የፖለቲካ አካል ወይም ዓለም አቀፍ ድርጅት ነው፡፡

3. **የግብር ከፋይ ደረጃዎች**

1. ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል የሚከተሉት የግብር ከፋይ ደረጃዎች ይኖራሉ፡፡

ሀ/የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋይ፡-

1. ድርጅት፤ ወይም
2. ጠቅላላ ዓመታዊ ገቢው ብር 1,000,000 (አንድ ሚሊዮን) ወይም ከዚህ በላይ የሆነ ማንኛውም ሌላ ሰው፤

ለ/ የደረጃ "ለ" ግብር ከፋይ የሚባለው ድርጅትን ሳይጨምር ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢው ከብር 1,000,000 (አንድ ሚሊዮን) የሚያንስ ነገር ግን ብር 500,000 (አምስት መቶ ሺህ) እና ከዚያ በላይ የሆነ ሰው፤

ሐ/ ደረጃ "ሐ" ግብር ከፋይ የሚባለው ድርጅትን ሳይጨምር ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢው ከብር 500,000 (አምስት መቶ ሺህ) የሚያንስ ሰው ነው፡፡

2. ቢሮው ታክስ ከፋዩ የሚያሳውቀውን ግብር ወይም የሚያገኘውን ሌላ መረጃ መሠረት በማድረግ ለግብር ዓመቱ የግብር ከፋዩ ደረጃ የተለወጠ መሆን አለመሆኑን ይወስናል፡፡

3. የፋይናንስ ቢሮ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከተውንና ግብር ከፋዮችን የደረጃ "ሀ"፣ የደረጃ "ለ" ወይም የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋይ ብሎ ለመመደብ የሚያስችለውን ዓመታዊ ጠቅላላ የገቢ መጠን በኢኮኖሚ ጥናት ላይ በመመስረት ቢያንስ በአምስት

organ of a government or an international organization.

**3. Categories of Taxpayer**

1. For the purposes of this Proclamation there shall be the following categories of taxpayers.

   a) category "A" taxpayer being

      1. a company ; or
      2. any other person having an annual gross income of Birr 1,000,000 or more;

   b) category "B" taxpayer being a person, other than a body , having an annual gross income of Birr 500,000 or more but less than 1,000,000;

   c) category "C" taxpayer being a person, other than a body, having an annual gross income of less than Birr 500,000.

2. The Bureau may, on the basis of tax declarations filed by a taxpayer or any other information available, determine whether the taxpayer's category has changed for a tax year.

3. The Finance Bureau shall, after ascertaining by economic analysis, change atleast within five years the annual gross income thresholds in sub-Article 1 of this Article for the classification of a taxpayer as a category "A" taxpayer or category "B" taxpayer or

ዓመት ጊዜ ውስጥ ማሻሻል አለበት፡፡

4. በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት

1. "በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት" የሚባለው ማናቸውም ሰው የንግድ ሥራውን በሙሉ ወይም በከፊል የሚያከናውንበት ቋሚ የንግድ ሥራ ቦታ ነው፡፡

2. ከዚህ በታች የተዘረዘሩት በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡

ሀ/ ዋነኛ ተግባሩ የድርጅቱ አገናኝ ሆኖ ከሚያገለግለው ጽህፈት ቤት በስተቀር የአስተዳደር ሥራ የሚከናወንበት ቦታ፣ ቢሮ፣ ፋብሪካ፣ መጋዘን ወይም ወርክሾፕ፤

ለ/ የማዕድን ማምረቻ ሥፍራ፣ የግንባታ ጠጠር ማምረቻ፣ ወይም ሌላ ማናቸውም የተፈጥሮ ሀብት ፍለጋ፣ ወይም ማምረት ሥራ የሚከናወንበት ቦታ፤

ሐ/ ለአንድ ወይም ለተያያዙ ፕሮጀክቶች በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ከ፩፻፹፫ (አንድ መቶ ሰማንያ ሶስት) ቀናት በላይ ለሆነ ጊዜ ተቀጣሪዎችን ወይም ሌሎች ሠራተኞችን በመመደብ የምክር አገልግሎትን ጨምሮ ሌሎች ማናቸውም አገልግሎቶች የሚሰጡበት ቦታ፤

3. የግንባታው ሥራ፣ ፕሮጀክቱ ወይም የሥራ እንቅስቀሴው ከ፩፻፹፫ (አንድ መቶ ሰማንያ ሶስት) ቀናት በላይ የሚቆይ እስከሆነ ድረስ የህንፃ ግንባታ ሥራ የሚከናወንበት ሥፍራ፣ የግንባታ፣ የመገጣጠም ወይም የተከላ ፕሮጀክት

category "C" taxpayer.

**4. Permanent Establishment**

1. "A permanent establishment" is a fixed place of business through which the business of a person is wholly or partly conducted.

2. The following are specifically treated as a permanent establishment:

a) a place of management, branch, office, factory, warehouse, or workshop, but does not include an office that has representation of the person's business as its sole activity;

b) a mine site, construction rock particle, quarry, or other place of exploration for, or extraction of, natural resources;

c) the furnishing of services, including consultancy services, by a person, including through employees or other personnel engaged by the person for such purpose, but only when activities of that nature continue for the same or a various project for a period more than one hundred eighty three days in any one-year period.

3. A building site, or a construction, assembly, or installation project, or supervisory activities connected with such site or project shall be a permanent establishment only when the site, project, or activities continue

ወይም ከእነዚህ ጋር የተገናኙ የቁጥጥር ሥራዎች በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተደነገገው ቢኖርም ራሱን ችሎ የሚሠራ ወኪል በመደበኛ የንግድ ሥራ አካሄድ ከሚያከናውነው ተግባር በስተቀር ማናቸውም ሰው "ወካይ" ተብሎ ለሚጠራ ሌላ ሰው ወኪል በመሆን በሌላ ሰው ስም የሚሰራ በሚሆንበት ጊዜ ወኪሉ የወካዩ በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት ነው የሚባለው፤

ሀ/ በወካዩ ስም በቋሚነት ውሎችን የሚደራደር፣ ወይም

ለ/ በወካዩ ስም የንግድ ዕቃዎችን ለማስረከብ አከማችቶ የሚይዝ ከሆነ ነው፡፡

5. በዚህ አንቀጽ "ራሱን ችሎ የሚሠራ ወኪል" ማለት በሚወክለው ሰው ቁጥጥር ስር ሳይሆን ራሱን ችሎ የሚሠራ ደላላ፣ የኮሚሽን ወኪል ወይም ሌላ ወኪል ሲሆን፣ የንግድ ወይም የፋይናንስ ግንኙነታቸው ራሳቸውን ችለው ከሚሠሩ ሰዎች የተለየ የሆነውን በብቸኝነት ወይም በዋነኛነት ለአንድ ሰው ወኪል በመሆን የሚሠሩትን አይጨምርም፡፡

5. **ነዋሪነት**

1. የሚከተሉት የኢትዮጵያ ነዋሪዎች ናቸው፡፡

ሀ/ ነዋሪ የሆነ ግለሰብ፣

for more than one hundred eighty three days.

4. Despite sub-articles (1) and (2) of this Article, when a person, other than an agent of independent status acting in the ordinary course of business, acts on behalf of another person (referred to as the “principal”), the first-mentioned person shall be a permanent establishment of the principal if the person:

(a) regularly negotiates contracts on behalf of the principal; or

(b) Maintains a stock of goods from which the person regularly delivers goods on behalf of the principal.

5. In this Article, “agent of independent status” means a broker, general commission agent, or other agent acting independently of the person that they represent, but does not include a person who acts solely or principally for another person if their commercial and financial relations differ from those that would have been made between independent person.

5. **Residence**

1/ The following are residents of Ethiopia:

ለ/ ነዋሪ የሆነ ድርጅት፣

ሐ/ የኢትዮጵያ መንግሥት እንዲሁም ማናቸውም የክልል መንግሥት ወይም የከተማ አስተዳደር፣

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) እንደተጠበቁ ሆነው፤ አንድ ግለሰብ በኢትዮጵያ ነዋሪ ነው የሚባለው፡-

ሀ/ በኢትዮጵያ ውስጥ ቋሚ የመኖሪያ አድራሻ ያለው፣

ለ/ የኢትዮጵያ ዜግነት ያለውና ከኢትዮጵያ ውጭ በኮንሱላር፣ በዲፕሎማቲክ ወይም በተመሳሳይ ሥራ ተመድቦ የሚሰራ፣

ሐ/ በኢትዮጵያ ውስጥ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ሳያቋርጥ ወይም በመመላለስ ከ፩፻፹፫ (አንድ መቶ ሰማንያ ሶስት) ቀናት በላይ የኖረ ግለሰብ፣

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት "የተያዘው የግብር ዓመት" ተብሎ ለሚጠቀሰው ለአንድ የግብር ዓመት ነዋሪ የሆነ ግለሰብ ባለፈው የግብር ዓመት ነዋሪ ያልሆነ እንደሆነ በተያዘው የግብር ዓመት እንደ ነዋሪ ሆኖ የሚቆጠረው ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ መኖር ከጀመረበት ቀን አንስቶ ነው፡፡

4. አንድ ግለሰብ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት በተያዘው የግብር ዓመት ነዋሪ

a) a resident individual;

b) a resident body;

c) the Government of Ethiopia, and any regional state or city government in Ethiopia.

2/ Subject to sub-Articles (3) and (4) of this Article, a resident individual is an individual who:

a) has a domicile in Ethiopia;

b) is a citizen of Ethiopia who is a consular, diplomatic, or similar official posted abroad;

c) is present in Ethiopia, continuously or intermittently, for more than 183 days in a one-year period.

3/ An individual who is a resident individual under sub-article (2) of this Article for a tax year (referred to as the “current tax year”), but who was not a resident individual for the preceding tax year shall be treated as a resident individual in the current tax year only for the period commencing on the day on which the individual was first present in Ethiopia.

4/ An individual who is a resident individual

ሆኖ፤ ነገር ግን በሚቀጥለው የግብር ዓመት ነዋሪ ያልሆነ እንደሆነ፤ በተያዘው የግብር ዓመት እንደ ነዋሪ ሆኖ የሚቆጠረው ግለሰቡ ለመጨረሻ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ ከኖረበት ቀን በፊት ላለው ጊዜ ነው፡፡

5. አንድ ድርጅት በኢትዮጵያ ነዋሪ ነው የሚባለው፡-

ሀ/ በኢትዮጵያ ውስጥ የተቋቋመ ወይም የተመሠረተ እንደሆነ፣

ለ/ ወሳኝ የሆነ አመራር የሚያካሂድበት ሥፍራ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው እንደሆነ፣ ነው፡፡

6. በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ድርጅት ነው፡፡

7. ነዋሪ ያልሆነ ሰው የሚባለው ማንኛውም በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ነው፡፡

**6. የገቢ ምንጭ**

1. አንድ ተቀጣሪ ከመቀጠር የሚያገኘው ገቢ በኢትዮጵያ የመነጨ ነው የሚባለው፡-

ሀ/ ክፍያው የሚፈጸምበት ሥፍራ ግምት ውስጥ ሳይገባ ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚከናወን የቅጥር አገልግሎት የተገኘ ገቢ፣ ወይም

ለ/ የቅጥር አገልግሎቱ የትም ቢከናወን በኢትዮጵያ መንግሥት ወይም በኢትዮጵያ መንግሥት ስም ክፍያው ለተቀጣሪው ከተፈፀመ ነው፡፡

under sub-article (2) of this Article for the current tax year but who is not a resident individual for the following tax year shall be treated as a resident individual in the current tax year only for the period ending on the last day on which the individual was present in Ethiopia.

5/ A resident body is abody that:

a) is incorporated or formed in Ethiopia; or

b) has its place of effective management in Ethiopia.

6/ A resident company is a company that is a resident body.

7/A non-resident is any person who is not a resident of Ethiopia.

**6. Source of Income**

1/ Employment income derived by an employee shall be Ethiopian source income:

a) to the extent that it is derived in respect of employment exercised in Ethiopia, wherever paid; or

b) if it is paid to the employee by, or on behalf of, the Government of Ethiopia, wherever the employment is exercised.

2. በቋሚነት በሚሠራ ድርጅቱ አማካይነት ከኢትዮጵያ ውጪ የሚያገኘውን ገቢ ሳይጨምር፤ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚያፈራው የንግድ ገቢ ከኢትዮጵያ ውስጥ የተገኘ ገቢ ይሆናል።

3. በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው የንግድ ሥራ ገቢ ኢትዮጵያ ውስጥ የተገኘ ነው የሚባለው፡-

ሀ/ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በቋሚነት በሚሰራ ድርጅት አማካይነት ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚያካሂደው የንግድ ሥራ የተገኘ ገቢ ሲሆን፣

ለ/ በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ያልሆነው ሰው በቋሚነት በሚሰራ ድርጅት አማካይነት ከሚሸጣቸው ዕቃዎች ወይም ሸቀጦች ጋር አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ የሆኑ እቃዎችን ወይም ሸቀጦችን ኢትዮጵያ ውስጥ በመሸጥ የሚያገኘው ገቢ፤

ሐ/ በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ያልሆነው ሰው በቋሚነት የሚሰራ ድርጅት ከሚያከናውናቸው የንግድ ሥራዎች ጋር አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ የሆኑ ሌሎች የንግድ እንቅስቃሴዎችን ኢትዮጵያ ውስጥ በማከናወን የሚያገኘው ገቢ፤

፬ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)፣ (፪) እና (፫) የተመለከተው ቢኖርም፣ የሚከተሉት

2/ Business income derived by a resident of Ethiopia shall be Ethiopian source income except to the extent that it is attributable to a business conducted by the resident through a permanent establishment outside Ethiopia.

3/ Business income derived by a non-resident shall be Ethiopian source income to the extent that it is attributable to:

a) a business conducted by the non-resident through a permanent establishment in Ethiopia;

b) sales in Ethiopia by the non-resident of goods or merchandise of the same or similar kind as those sold by the non-resident through a permanent establishment in Ethiopia; or

c) any other business activity conducted by the non-resident in Ethiopia of the same or similar kind as that conducted by the non-resident through a permanent establishment in Ethiopia.

ገቢዎች ኢትዮጵያ ውስጥ የመነጩ ገቢዎች ናቸው፡-

ሀ/ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ድርጅት ለአንድ ሰው የሚከፍለው የትርፍ ድርሻ፣

ለ/ የሚከተሉትን ንብረቶች በማከራየት የሚገኝ ገቢ፣

1. በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ የማይንቀሳቀስ ንብረት ወይም

2. በአንቀጽ ፶፮ መሠረት ግብር የሚከፈልበት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ የሚንቀሳቀስ ንብረት፣

ሐ/ የሚከተሉትን ንብረቶች በማስተላለፍ የሚገኝ ገቢ፡-

፩ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ የማይንቀሳቀስ ንብረት፣

2. ከ፶% በላይ በሚሆነው በንብረቱ ዋጋ ላይ ያለው ጥቅም በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ የተዛመዱ ድርጅቶች የተያዘ በሚሆንበት ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ያለ ጥቅም፣

3. በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ ያወጣው አክሲዮን ወይም ቦንድ፤

መ/ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ መድን ለተገባለት አደጋ (ስጋት) የሚከፈል የመድን አረቦን፣

4/ Despite sub-articles (1), (2), and (3) of this Article, income derived by a person shall be Ethiopian source income if it is:

a) a dividend paid to the person by a resident body;

b) rental income from the lease of:

(1) immovable property located in Ethiopia; or

(2) movable property located in Ethiopia subject to tax under Article 56 of this Proclamation;

c) a gain arising from the transfer of the following:

(1) immovable property located in Ethiopia;

(2) a membership interest in a body, if more than 50% of the value of the interest is derived, directly or indirectly through one or more interposed bodies, from immovable property located in Ethiopia;

(3) shares in, or bonds issued by, a resident company;

d) an insurance compensation relating

ሠ/ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚከናወን የመዝናኛ ወይም ስፖርታዊ እንቅስቃሴ የሚገኝ ገቢ፣

ረ/ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚካሄዱ የዕድል ሙከራዎችን በማሸነፍ የሚገኝ ገቢ፣

ሰ/ በዚህ አዋጅ መሠረት ግብር የሚከፈልበትን ወለድ፣ ሮያሊቲ፣ የሥራ አመራር ክፍያ ወይም የቴክኒክ አገልግሎት ክፍያ በሚመለከት፡-

1. በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነው ሰው በቋሚ ድርጅቱ አማካይነት ውጭ ሀገር ለሚያካሂደው የንግድ ሥራ ያወጣውን ወጪ ሳይጨምር፣ በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆነ ሰው የሚፈጽመው ክፍያ፤
2. በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው በቋሚነት በሚሰራ ድርጅት አማካይነት በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚያካሂደው የንግድ ሥራ የሚፈጽመው ክፍያ፤

፭ ከኢትዮጵያ ውስጥ ያልመነጨ ማንኛውም ገቢ የውጭ ሀገር ገቢ ነው፡፡

7. **የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሕገ መንግስት መሠረት ለክልሉ መንግስት ተለይተው በተሰጡ ገቢዎች የክልሉ ግብር ከፋይ የሆኑና በሕግ አግባብ ግብር መክፈል ያለባቸው ግብር ከፋዮች በክልሉ ውስጥም ሆነ ከክልሉ ውጪ ባገኙት ማናቸውም ገቢ ላይ

to the insurance of a risk in Ethiopia;

e) income from a performance or sporting event taking place in Ethiopia;

f) winnings from a game of chance held in Ethiopia;

g) interest, a royalty, management fee, technical fee, or other income subject to tax under this Proclamation:

1) paid to the person by a resident of Ethiopia, other than as an expenditure of a business conducted by the resident through a permanent establishment outside Ethiopia; or

2) paid by a non-resident as an expenditure of a business conducted by the non-resident person through a permanent establishment in Ethiopia.

5. Foreign income is any income that is not Ethiopian source income.

7. **Scope of Application**

This Proclamation shall apply on every income derived, by the Region taxpayer and those have to pay tax on the pertinent law, in the Region or else outside the Region, on income identified, for the Region

ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

8. **የገቢ ሠንጠረዦች**

፩ በዚህ አዋጅ የተደነገገው የገቢ ግብር በሚከተሉት ሠንጠረዦች መሠረት ይከፈላል፡፡

ሀ/ ሠንጠረዥ "ሀ" ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ፤

ለ/ሠንጠረዥ "ለ" ከቤት ኪራይ የሚገኝ ገቢ፤

ሐ/ ሠንጠረዥ "ሐ" ከንግድ ሥራ የሚገኝ ገቢ፤

መ/ ሠንጠረዥ "መ" ሌሎች ገቢዎች፤

ሠ/ ሠንጠረዥ "ሠ" ከገቢ ግብር ነፃ የሆኑ ገቢዎች፤

፪ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፪ (፪) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ግብር ከፋዩ በግብር ዓመቱ በአንድ ሠንጠረዥ ውስጥ ከሚወድቁ ከተለያዩ የገቢ ምንጮች ገቢ ያገኘ እንደሆነ ሁሉም ገቢዎች ተጣምረው በዚያው ሠንጠረዥ ሥር የዓመቱን ግብር ይከፍላል፡፡

9. **የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ**

ማንኛውም ገቢ የሚያገኝ ሰው በዚህ አዋጅና በክልሉ የታክስ አስተዳደር አዋጅ መሠረት ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

government according to the Ethiopian Federal Democratic Constitution.

8. **Schedules of Income**

1. The Proclamation provides for the taxation of income in accordance with the following schedules:
    a) Schedule ‘A’, income from employment;
    b) Schedule ‘B’, income from rental of buildings;
    c) Schedule ‘C’, income from business;
    d) Schedule ‘D’, other income;
    e) Schedule ‘E’, exempt income.
2. Subject to Article 62 (2) of this Proclamation, a taxpayer that derives income from different sources subject to tax under the same Schedule for a tax year shall be taxable under the Schedule on the total income for the year.

9. **Obligation to Pay Income Tax**

Every person deriving income shall pay income tax in accordance with this Proclamation and the Tax Administration Proclamation.

## ክፍል ሁለት

## ሠንጠረዥ "ሀ" ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ

### ፲.ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ስለመጣል

1. በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፹፪ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማናቸውም ተቀጣሪ በአንድ ወር ውስጥ ከመቀጠር ከሚያገኘው ጠቅላላ የወር ወይም የወሩ ከፊል ገቢ ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ በተወሰኑት ምጣኔዎች መሠረት በእያንዳንዱ ወር ግብር ይከፍላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ከመቀጠር በሚገኝ ወርሀዊ ገቢ ላይ የሚጣለው የገቢ ግብር ተቀጣሪው በአንድ ወር ውስጥ በሚያገኘው ጠቅላላ ወርሃዊ ገቢ ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ መሠረት ተፈጻሚ የሚሆነውን ምጣኔ መሠረት በማድረግ ይሰላል፡፡
3. ተቀጣሪው በመቀጠር የሚገኘውን ገቢ ለማግኘት የሚያወጣው ማንኛውም ወጪ በተቀናሽ ሊያዝለት አይችልም፡፡
4. ለዚህ ሠንጠረዥና ለዚህ አዋጅ አንቀጽ ፹፬ አፈጻፀም ሲባል፤ በነሐሴና በጳጉሜን ወራት የሚከፈለው የቅጥር ገቢ ተደምሮ እንደ አንድ ወር ደመወዝ ግብር ይከፈልበታል፡፡
5. በአንድ ተቀጣሪ ላይ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፹፩ (፩) ድንጋጌ ተፈጻሚ የተደረገ እንደሆነ በመቀጠር በተገኘው ገቢ ላይ ተቀጣሪው የከፈለው ታክስ የመጨረሻ ይሆናል፡፡ ቀጣሪው በአንቀጽ ፹፬ መሠረት ከተቀጣሪው

## PART TWO

## SCHEDULE 'A' INCOME FROM EMPLOYMENT

### 10. Imposition of Employment Income Tax

1. Without prejudice to Article 82 of this Proclamation, Employment income tax shall be imposed for each calendar month or part thereof at the rate or rates specified in Article 11of this Proclamation on an employee who receives employment income during the month or part thereof.
2. The employment income tax imposed on an employee under sub-article (1) of this Article for a month shall be calculated by applying the rate or rates of tax applicable to the employee under Article 11of this Proclamation to the total employment income received by the employee for the month.
3. An employee shall not be allowed a deduction for any expenditure incurred in deriving employment income.
4. For the purposes of this Schedule and Article 84 of this Proclamation, the employment income attributable to the months of Nehassie and Pagumen shall be aggregated and treated as the employment income of a single calendar month.
5. If Article 81 (1) applies to an employee, the employment income tax payable by the employee shall be a final tax on the employment income of the employee and the tax shall be discharged if the employer has

የሚፈለገውን የገቢ ግብር ቀንሶ ያስቀረ እንደሆነ ግብሩ እንደተከፈለ ይቆጠራል፡፡

withheld tax from the income in accordance with Article 84 of this Proclamation.

**01. በመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ ምጣኔዎች**

ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ ለሚጣለው ግብር ተፈጻሚ የሚሆኑት ምጣኔዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

| በየወሩ ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ በብር | ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ምጣኔ |
|---|---|
| 0-600 | 0% |
| 601-1,650 | 10% |
| 1,651-3,200 | 15% |
| 3,201-5,250 | 20% |
| 5,251-7,800 | 25% |
| 7,801-10,900 | 30% |
| ከ10,900 በላይ | 35% |

**11. Employment Income Tax Rates**

The rates of employment income tax are:

| Employment Income (per month) Birr | Employment Income Tax Rate |
|---|---|
| 0 –600 | 0% |
| 601-1,650 | 10% |
| 1,651-3,200 | 15% |
| 3,201-5,250 | 20% |
| 5,251-7,800 | 25% |
| 7,801-10,900 | 30% |
| Over 10,900 | 35% |

**02. ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ**

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ከመቀጠር የሚገኙ ገቢዎች ናቸው የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ/ ሠራተኛው ካለፈው፣ አሁን ካለው ወይም ወደፊት ከሚመጣው የቅጥር ውል ጋር በተያያዘ የሚያገኘው ደመወዝ፣ ምንዳ፣ አበል፣ ጉርሻ፣ ኮሚሽን፣ የመልካም ሥራ አፈፃፀም ማበረታቻ ስጦታ ወይም ሌላ የአገልግሎት ዋጋ ክፍያ፤

ለ/ ያለፈን፣ የአሁኑን ወይም የወደፊትን

**12. Employment Income**

1. Subject to sub-articles (2) and (3) of this Article, employment income means the following:

   a) salary, wages, an allowance, bonus, commission, gratuity, or other remuneration received by an employee in respect of a past, current, or future employment;

ቅጥር አስመልክቶ ሠራተኛው የሚያገኘው የዓይነት ጥቅማ ጥቅም ዋጋ፤

ሐ/ ተቀጣሪው ከሥራ ሲቀነስ፣ ሥራውን ሲለቅ ወይም እንዲለቅ ለማግባባት የሚከፈል ገንዘብን ጨምሮ የሥራ ውል በመቋረጡ ምክንያት በፈቃደኝነት፣ በስምምነት ወይም በዳኝነት ውሳኔ መሠረት የተቀበለው ማንኛውም የገንዘብ መጠን፤

2. በመቀጠር የሚገኝ ገቢ ከግብር ነፃ የተደረገን ገቢ አይጨምርም።

3. ማንኛውም ቀጣሪ ተቀጣሪው መክፈል የሚኖርበትን ግብር ከተቀጣሪው ገቢ ላይ ሳይቀንስ ራሱ ለተቀጣሪው በሙሉ ወይም በከፊል የከፈለለት እንደሆነ፣ በቀጣሪው የተከፈለው የግብር መጠን ተቀጣሪው ከመቀጠር ከሚያገኘው ግብር በሚከፈልበት የገንዘብ መጠን ላይ ተደምሮ ግብሩ ይሰላል።

4. የመስተዳደር ምክር ቤት ከደመወዝ ሌላ በዓይነት የሚሰጡ ጥቅማጥቅሞች ዋጋ የሚወሰንበትንና ግብር የሚከፈልበትን ሁኔታ አስመልክቶ ደንብ ያወጣል።

## ክፍል ሦስት
## ሠንጠረዥ "ለ" ከቤት ኪራይ የሚገኝ ገቢ

### 03. በቤት ኪራይ ገቢ ላይ ግብር ስለመጣል

1. ቤት በማከራየት ገቢ የሚያገኝ ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፬ በተመለከተው ምጣኔ ወይም ምጣኔዎች መሠረት በእያንዳንዱ

b) the value of fringe benefits received by an employee in respect of a past, current, or future employment;

c) an amount received by an employee on termination of employment, whether paid voluntarily, under an agreement, or as a result of legal proceedings, including any compensation for redundancy or loss of employment, or a golden handshake payment.

2. Employment income shall not include exempt income.

3. If an employer pays the employment income tax payable by an employee, in whole or part, without withholding tax from the employment income of the employee, the amount of tax paid by the employer shall be included in the employment income of the employee.

4. The Executive Council shall make Regulations for determining the value and taxation of fringe benefits.

## PART THREE
## SCHEDULE 'B' – INCOME FROM RENTAL OF BUILDINGS

### 13. Imposition of Rental Income Tax

1. Rental income tax shall be imposed for each tax year at the rate or rates specified in Article 14of this Proclamation on a person renting

የግብር ዓመት የቤት ኪራይ ገቢ ግብር ይከፍላል፡፡

2. በግብር ዓመቱ አንድ ግብር ከፋይ ከቤት ኪራይ በሚያገኘው ገቢ ላይ የሚከፈለው ግብር በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፬ ሥር የተመለከቱትን ምጣኔዎች ግብር በሚከፈልበት ዓመታዊ ገቢ ላይ ተፈፃሚ በማድረግ ይሰላል፡፡
3. ይህ ሠንጠረዥ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፮ መሠረት የኪራይ ገቢ ግብር ለሚከፈልበት ገቢ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## ፲፬ የኪራይ ገቢ ግብር ምጣኔዎች

1. በድርጅቶች የኪራይ ገቢ ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው የግብርምጣኔ ፴ በመቶ ነው፡፡
2. በግለሰቦች የኪራይ ገቢ ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑት ምጣኔዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

| ግብር የሚከፈልበት የኪራይ ገቢ በዓመት | የኪራይ ግብር ምጣኔ |
|---|---|
| 0-7,200 | 0% |
| 7,201-19,800 | 10% |
| 19,801-38,400 | 15% |
| 38,401-63,000 | 20% |
| 63,001-93,6 0 | 25% |
| 93,601-130,800 | 30% |
| ከ130,800 በላይ | 35% |

out a building or buildings who has taxable rental income for the year.

2. The rental income tax payable by a taxpayer for a tax year shall be calculated by applying the rate or rates of tax applicable to the taxpayer under Article 14of this Proclamation to the taxable rental income of the taxpayer for the year.
3. This Schedule shall not apply to rental income subject to tax under Article 56.

## 14. Rental Income Tax Rates

1. The rate of rental income tax applicable to a body is 30%.
2. The rates of rental income tax applicable to an individual are:

| **Taxable Rental Income (per year) Birr** | **Rental Income Tax Rate** |
|---|---|
| 0 -7,200 | 0% |
| 7,201-19,800 | 10% |
| 19,801-38,400 | 15% |
| 38,401-63,000 | 20% |
| 63,001-93,600 | 25% |
| 93,601-130,800 | 30% |
| Over 130,800 | 35% |

**፲፭ግብር የሚከፈልበት የኪራይ ገቢ**

1. የአንድ ግብር ከፋይ ግብር የሚከፈልበት ዓመታዊ የኪራይ ገቢ ነው የሚባለው ግብር ከፋዩ በዓመቱ ውስጥ ቤት ወይም ቤቶችን በማከራየት ካገኘው ጠቅላላ ዓመታዊ ገቢ ላይ ለግብር ከፋዩ የተፈቀደው ጠቅላላ ወጪ ተቀናሽ ተደርጎ የሚቀረው ገቢ ነው፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) እንደተጠበቁ ሆነው፣ አንድ ግብር ከፋይ በግብር ዓመቱ ቤት ወይም ቤቶችን በማከራየት የሚያገኘው ጠቅላላ ገቢ የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

ሀ/ የኪራይ ዋጋ ጭማሪን ወይም ተመሳሳይ ክፍያዎችን ጨምሮ፣ በኪራይ ውሉ መሠረት ታክስ ከፋዩ በዓመቱ የሚያገኛቸው ማናቸውም የገንዘብ መጠን፣

ለ/ በኪራይ ውሉ መሠረት ተከራዩ አከራዩን በመወከል በግብር ዓመቱ ለሌሎች የሚከፍላቸው ክፍያዎች፤

ሐ/ ግብር ከፋዩ ጉዳቱን ለማስተካከል ያልተጠቀመበት እና በቤቱ ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ማስተካከያ ይሆን ዘንድ የያዘው እና በግብር ዓመቱ ለግብር ከፋዩ ገቢ የተደረገው ማንኛውም ቦንድ፣ ዋስትና ወይም ተመሳሳይ ገንዘብ፤

መ/ ለታክስ ከፋዩ ከሚከፈለው ኪራይ በተጨማሪ በኪራዩ ውል መሠረት

**15. Taxable Rental Income**

1. The taxable rental income of a taxpayer for a tax year is the gross amount of income derived by the taxpayer from the rental of a building or buildings for the year reduced by the total amount of deductions allowed to the taxpayer for the year.
2. Subject to sub-articles (3) and (4) of this Article, the gross amount of income derived by a taxpayer from the rental of a building for a tax year shall include the following:

a) all amounts derived by the tax payer during the year under the lease agreement, including any lease premium or similar amount;

b) all payments made by the lessee during the year on behalf of the lessor according to the lease agreement;

c) the amount of any bond, security, or similar amount that, during the year, the taxpayer is entitled to retain as a result of damage to the building and that has not been used by the taxpayer in repairing the damage to the building;

d) the value of any renovation or improvement made under the lease

ተከራዩ ራሱ ለቤቱ እድሳት ወይም ማሻሻያ የሚያወጣው ገንዘብ፤

3. ግብር ከፋዩ ቤቱን ያከራየው ከዕቃዎች ጋር በሚሆንበት ጊዜ፣ ግብር ከፋዩ ያገኘው ጠቅላላ ገቢ ከዕቃዎቹ የተገኘውን የኪራይ ገቢም ያጠቃልላል፡፡

4. ግብር ከፋዩ ቤት በማከራየት የሚያገኘው ጠቅላላ ገቢ ከገቢ ግብር ነጻ የሆነን ገቢ አይጨምርም፡፡

5. በአንድ የግብር ዓመት የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ የሌለበት ግብር ከፋይ ግብር የሚከፈልበት ገቢ በሚሰላበት ጊዜ የሚከተሉት ወጪዎች በተቀናሽ ይያዛሉ፡-

ሀ/ ታክስን ሳይጨምር ለመሬቱ ወይም ከተከራየው ቤት ጋር በተገናኘ ግብር ከፋዩ ለመንግሥት ወይም ለከተማ አስተዳደር በግብር ዓመቱ ውስጥ የከፈላቸው ክፍያዎች፤

ለ/ ለቤቶች፣ ለቤት ዕቃና መሣሪያ ማደሻ፣ መጠገኛና ለእርጅና መተኪያ የሚሆን ከቤት፣ ከቤት ዕቃ እና ከመሳሪያ ኪራይ ከሚገኘው ጠቅላላ ገንዘብ ላይ ሃምሳ በመቶ፤

6. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፭ ድንጋጌ በማናቸውም ምክንያት በዚህ አዋጅ መሠረት የሂሣብ መዝገብ የመያዘ ግዴታ ላለባቸው ግብር ከፋዮች ተፈፃሚ ሊሆን አይችልም፡፡

agreement to the building when the cost was borne by the lessee in addition to the rent payable to the taxpayer.

3. If a taxpayer leases a furnished building, the gross amount of income derived by the taxpayer from the lease of the building shall include any amount attributable to the lease of the furniture or equipment.

4. The gross amount of income derived by a taxpayer from the lease of a building shall not include exempt income.

5. In computing the taxable rental income for a tax year of a taxpayer who does not maintain books of account,a deduction shall be allowed for the following amounts:

a) any fees and charges, but not tax, levied by a government or city administration in respect of the land or building leased and paid by the taxpayer during the year;

b) an amount equal to fifty percent (50%) of the gross rental income derived by the taxpayer for the year as an allowance for the repair, maintenance, and depreciation of the building, furniture, and equipment.

6. The provisions of sub-article 5 of this Article shall not be applicable for taxpayers who are required to maintain books of account under this Proclamation, for any reason what so ever.

7. የሂሳብ መዝገብ የሚይዝ ግብር ከፋይ የዓመቱ ግብር የሚከፈልበት ገቢ በሚሰላበት ጊዜ ገቢውን ለማግኘት የወጣና በታክስ ከፋዩ የተከፈለ ወጪ ተቀናሽ የሚደረግ ሲሆን፣ ይህም ወጪ የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

ሀ/ ቤቱ ያረፈበት መሬት ኪራይ፤

ለ/ የጥገና ወጪ፤

ሐ/የቤቱ፣ የቤት ዕቃዎችና የመሣሪያዎች የእርጅና ቅናሽ፤

መ/ ወለድና የመድን አረቦን፤

ሠ/ ታክስን ሳይጨምር ለመሬቱ ወይም ከተከራየው ቤት ጋር በተገናኘ ግብር ከፋዩ ለመንግሥት ወይም ለከተማ አስተዳደር የከፈላቸው ክፍያዎች፤

06. የተከራይ አከራዮች

1. የተከራይ አከራይ በግብር ዓመቱ ያገኘው ግብር የሚከፈልበት ገቢ ነው የሚባለው የተከራይ አከራዩ በግብር ዓመቱ ከሚያገኘው ጠቅላላ የኪራይ ገቢ ላይ ለዋናው አከራይ የሚከፍለው ኪራይ እንዲሁም ገቢውን ለማግኘት ያወጣቸው ሌሎች አስፈላጊ ወጪዎች ከተቀነሱ በኋላ የሚቀረው ገንዘብ ነው፡፡

2. ተከራይ የተከራየውን ቤት መልሶ እንዲያከራይ የሚፈቅድ የቤት ባለቤት ተከራዩ ግብሩን ሳይከፍል ቢቀር ስለእርሱ ሆኖ ግብሩን የመክፈል ኃላፊነት

7. In computing the taxable rental income for a tax year of a taxpayer who maintains books of account, a deduction shall be allowed for any expenditures to the extent necessarily incurred by the taxpayer in deriving rental income and paid during the year including:

a) the cost of the lease of land on which the building is situated;

b) maintenance expenditure;

c) depreciation of the building,furniture and equipment;

d) interest and insurance premiums; and

e) fees and charges, but not tax, levied by a State or city administration in respect of the land or building leased.

**16. Sub-leases**

1. The taxable rental income of a sub-lessor of a building for a tax year shall be the difference between the total rental income received by the sub-lessor during the year and the total rental income paid to the lessor of the building plus other expenses to the extent necessarily incurred by the sub lessor to generate the income.

2. The owner of a building who allows a lessee to sub-lease the building shall be liable for the rental income tax payable by

ይኖርበታል፡፡

07. **የሚከራይ አዲስ ቤትን ስለማሳወቅ**

1. ለኪራይ የሚሰራ ቤት ተሰርቶ እንዳለቀ ወይም ቤቱ እንደተከራየ፣ ከሁለቱ በሚቀድመው ጊዜ የቤቱ ባለቤትና የቤቱ ሥራ ተቋራጭ የቤቱ ግንባታ የተጠናቀቀ ወይም የተከራየ መሆኑን ከቤቱ ኪራይ በሚገኘው ገቢ ላይ የሚፈለገውን ግብር መክፈል ያለበትን ሰው ስም፣ አድራሻና የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር፣ ቤቱ ለሚገኝበት የቀበሌ አስተዳደር በ፲፭ ቀናት ውስጥ ማስታወቅ አለበት፡፡
2. የቀበሌው አስተዳደር እና የአካባቢው አስተዳደር በማስታወቂያው መሠረት የተገኘውን መረጃ በ፲፭ ቀናት ውስጥ ለቢሮው መግለጽ አለበት፡፡

**ክፍል አራት**

**ሠንጠረዥ "ሐ" ከንግድ ሥራ የሚገኝ ገቢ**

**ምዕራፍ አንድ**

**ከንግድ ሥራዎች በሚገኝ ገቢ ላይ ግብርን ስለመጣል**

08. **በንግድ ሥራ ገቢ ላይ ግብርን ስለመጣል**

1. በዚህ ክፍል የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በግብር ዓመቱ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ያለው ሰው በእያንዳንዱ የግብር ዓመት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፱ በተመለከተው ምጣኔ ወይም ምጣኔዎች መሠረት የንግድ ሥራ ገቢ ግብር ይከፍላል፡፡

the lessee if the lessee fails to pay the tax.

**17. New Rental Building Notification**

1. At the earlier of the time construction of a rental building is completed or when the building is rented, the owner of the building and the builder shall notify the kebele administration and local administration in which the building is located about the completion and the name, address, and TIN of the person liable for rental income tax with respect to the building in 15 days.
2. The kebele administration and local administration shall communicate the information contained in the notification within 15 days to the Bureau.

**PART FOUR**

**SCHEDULE ‘C’ INCOME FROM BUSINESS**

**CHAPTER ONE**

**IMPOSITION OF BUSINESS INCOME TAX**

**18. Imposition of Business Income Tax**

1. Subject to the provisions of this Part, business income taxshall be imposed for each tax year at the rate or rates specified in Article 19of this Proclamation on a personconducting business that has taxable income for the year.

2. አንድ ግብር ከፋይ በአንድ የግብር ዓመት የሚከፍለው የንግድ ሥራ ገቢ ግብር የሚሰላው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፱ የተመለከተው ምጣኔ ወይም ምጣኔዎች በግብር ከፋዩ የዓመቱ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ላይ ተፈፃሚ እንዲሆኑ በማድረግ ነው፡፡

**፲፱. በንግድ ሥራ ገቢ ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ ምጣኔዎች**

1. በድርጅት ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው የንግድ ሥራ ገቢ የግብር ምጣኔ ሰላሳ በመቶ (፴%) ነው፡፡

2. በግለሰብ ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑት የንግድ ሥራ ገቢ ግብር ምጣኔዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

| ከንግድ ሥራ የሚገኝ ግብር የሚከፈልበት ገቢ በዓመት | የንግድ ሥራ ገቢ የግብር ምጣኔ |
|---|---|
| 0-7,200 | 0% |
| 7,201-19,800 | 10% |
| 19,801-38,400 | 15% |
| 38,401-63,000 | 20% |
| 63,001-93,600 | 25% |
| 93,601-130,800 | 30% |
| ከ130,800 በላይ | 35% |

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ድንጋጌ ቢኖርም ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ግብር የሚከፍሉት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ

2. The business income tax payable by a taxpayer for a tax year shall be calculated by applying the rate or rates of tax applicable to the taxpayer under Article 19 of this Proclamation to the taxable income of the taxpayer for the year.

**19. Business Income Tax Rates**

1. The rate of business income tax applicable to a body is [30%].

2. The rates of business income tax applicable to an individual are:

| Taxable Business Income (per year) Birr | Business Income Tax Rate |
|---|---|
| 0 - 7,200 | 0% |
| 7,201-19,800 | 10% |
| 19,801-38,400 | 15% |
| 38,401-63,000 | 20% |
| 63,001-93,600 | 25% |
| 93,601-130,800 | 30% |
| Over 130,800 | 35% |

3. Notwithstanding sub-article (1) of this Article Micro Enterprises shall pay income tax in accordance with rates

፪ ሥር በተመለከቱት ምጣኔዎች መሠረት ይሆናል፡፡

4. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ አፈፃፀም "ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ” የሚለው የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድና ኢንዱስትሪ የገበያ ዕድል ለማስፋፋትና ለማበረታታት በሚወጣው የመስተዳድር ምክር ቤት ደንብ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡

**፳ ግብር የሚከፈልበት የንግድ ሥራ ገቢ**

1. የአንድ ግብር ከፋይ ግብር የሚከፈልበት ዓመታዊ የንግድ ሥራ ገቢ ነው የሚባለው ከንግድ ሥራ ከተገኘ ጠቅላላ ዓመታዊ ገቢ ላይ ለግብር ከፋዩ የተፈቀዱት ወጪዎች ተቀናሽ ከተደረጉ በኋላ የሚገኘው የገቢ መጠን ነው፡፡

2. በዚህ አዋጅ የመስተዳደር ምክር ቤት በሚያወጣቸው ደንቦች እና ፋይናንስ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ የሚደረጉ ማሻሻያዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የአንድ ግብር ከፋይ ግብር የሚከፈልበት ዓመታዊ ገቢ የሚወሰነው ግብር ከፋዩ በፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች መሠረት በሚያዘጋጀው የትርፍና ኪሳራ ወይም ገቢ መግለጫ ላይ በመመስረት ይሆናል፡፡

**፳፩ የንግድ ሥራ ገቢ**

1. በዚህ አዋጅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በአንድ የግብር ዓመት የአንድ

prescribed under sub-article (2) of this Article.

4. For the purpose of sub article (3) of this Article “Micro Enterprises” shall have the meaning provided under the Regulation to be issued to expand and promote the market opportunity of micro and small business industry of the Central Ethiopia Region State.

**20. Taxable Business Income**

1. The taxable business income of a taxpayer for a tax year shall be the total business income of the taxpayer for the year reduced by the total deductions allowed to the taxpayer for the year.

2. The taxable business income of a taxpayer for a tax year shall be determined in accordance with the profit and loss, or income statement, of the taxpayer for the year prepared in accordance with the financial reporting standards, subject to the Regulations issued by the Executive Council and the amendment made on Directives issued by the Finance Bureau under this Proclamation.

**21. Business Income**

1. Subject to the provisions of this Proclamation, the business income of a taxpayer for a tax year shall

የንግድ ሥራ ገቢ ግብር ከፋይ የንግድ ሥራ ገቢ የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

ሀ/ ከመቀጠር የሚገኝ ገቢን ሳይጨምር ግብር ከፋዩ ዕቃዎችን በመሸጥና በመለወጥ እንዲሁም አገልግሎቶችን በመስጠት የሚያገኘውን የገንዘብ መጠን ጨምሮ በግብር ዓመቱ ከንግድ ሥራ ያገኘው ጠቅላላ ገንዘብ መጠን፤

ለ/ ለንግድ የሚውል ዕቃን ሳይጨምር በግብር ዓመቱ የንግድ ሥራ ሀብትን በማስተላለፍ የሚገኝ የገንዘብ መጠን፤

ሐ/ በዚህ አዋጅ መሠረት ለግብር ዓመቱ የግብር ከፋዩ ገቢ ተደርጎ የሚወሰድ ሌላ ማንኛውም የገንዘብ መጠን፤

2. ከንግድ ሥራ የሚገኝ ገቢ ከገቢ ግብር ነፃ የተደረገን ገቢ አይጨምርም፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩(ለ) መሠረት በንግድ ሥራ ገቢ ውስጥ የሚካተተው የንግድ ሥራ ሀብትን በማስተላለፍ የሚገኝ ገቢ ከንግድ ሥራ ሀብቱ የመዝገብ ዋጋ በላይ የሆነው የንግድ ሥራ ሀብቱ በሚተላለፍበት ጊዜ ከተላለፈው ሀብት የተገኘው ገቢ ነው፡፡

4. አንድ የንግድ ሥራ ሀብት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፯ መሠረት ግብር የሚከፈልበት ከሆነ፡-

ሀ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩(ለ)

include the following:

a) the gross amountsderived by the taxpayer during the year from the conduct of a business, including the gross proceeds from the disposal of trading stock and the gross fees for the provision of services (other than employment income);

b) a gain on disposal of a business asset (other than trading stock) made by the taxpayer during the tax year;

c) any other amount included in business incomeof the taxpayer for the tax year under this Proclamation.

2. Business income shall not include an amount that is exempt income.

3. Subject to sub-article (4) of this Article, the gain on disposal of a business asset included in business income under sub-article (1)(b) of this Article is the amount by which the consideration for the disposal of the asset exceeds the net book value of the asset at the time of disposal.

4. If a business asset is a taxable asset under Article 57 of this Proclamation:

መሠረት በንግድ ሥራ ገቢ ውስጥ የሚካተተውን የንግድ ሥራ ሀብትን በማስተላለፍ የሚገኘውን ገቢ ለንግድ ሥራው ሀብት የተደረገው ወጪ ከንግድ ሥራው ሀብት የተጣራ የመዝገብ ዋጋ በሚበልጠው የገንዘብ መጠን ሲሆን፤

ለ/ ከወጪው በላይ በሚገኘው ጥቅም ላይ በአንቀጽ ፶፯ መሠረት ግብር ይከፈልበታል፡፡

## ፳፪ ተቀናሽ የሚደረጉ ወጪዎች

1. የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ በግብር ዓመቱ የግብር ከፋዩን ግብር የሚከፈልበት ገቢ ለመወሰን በተቀናሽ የሚያዙት ወጪዎች የሚከተሉትን ይጨምራሉ፡-

ሀ/ በንግድ ገቢው ውስጥ የተካተቱትን ገቢዎች ለማግኘት፣ ለንግዱ ዋስትና ለመስጠትና የንግድ ሥራውን ለማስቀጠል በግብር ከፋዩ በግብር ዓመቱ ውስጥ የተደረጉ አስፈላጊ የሆኑ ወጪዎች፤

ለ/ በፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች በተመለከተው መሠረት የተሠላ በግብር ዓመቱ በግብር ከፋዩ ለተሸጠ የንግድ ዕቃ የወጣ ወጪ፤

ሐ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፭ በሚወሰነው መሠረት የንግድ ገቢን

a) the gain on disposal of the asset included in business income under sub-article (1)(b) of this Article is the amount (if any) by which the cost of the asset exceeds the net book value of the asset at the time of disposal; and

b) any gain above cost is taxable under Article 57.

## 22. Deductible Expenditures

1. Subject to the provisions of this Proclamation, in determining the taxable income of a taxpayer for a tax year, the deductions allowed to a taxpayer shall include the following:

a) any expenditure to the extent necessarily incurred by the taxpayer during the year in deriving, securing, and maintaining amounts included in business income;

b) the cost of trading stock disposed of by the taxpayer during the year as determined in accordance with the financial reporting standards;

c) the total amount by which the depreciable assets and business

ለማግኘት ሥራ ላይ የዋሉ ዋጋቸው የሚቀንስ ንብረቶች እና ግዙፋዊ ህልዎት ለሌላቸው የንግድ ሀብቶች በግብር ዓመቱ የሚታሰበው ጠቅላላ የእርጅና ቅናሽ፤

መ/ ግብር ከፋዩ የንግድ ዕቃን ሳይጨምር በግብር ዘመኑ የንግድ ሥራ ሀብትን ሲያስተላልፍ የሚገጥመው ኪሳራ፤

ሠ/ ለግብር ዘመኑ በዚህ አዋጅ መሠረት ለግብር ከፋዩ በተቀናሽነት የሚፈቀድ ሌላ ማናቸውም ወጪ፤

2. ግብር የሚከፈልበት ሃብት ዋጋው የሚቀንስ ሀብት ካልሆነ በስተቀር፣ ግብር የሚከፈልበት ሃብት በሚተላለፍበት ጊዜ ለሚደርስ ኪሳራ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፯ ተፈጻሚ የሚሆን ሲሆን፣ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) (መ) ግን ተፈጻሚ አይሆንም።

3. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩(መ) አፈጻፀም፤ የንግድ ሀብትን በማስተላለፍ የሚደርስ ኪሳራ የሚባለው ሀብቱ በተሸጠበት ጊዜ የሀብቱ የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ሀብቱ ከተላለፈበት ዋጋ በሚበልጠው የገንዘብ ልክ ነው።

**፳፫ የወለድ ወጪ**

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ እና የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፯ እንደተጠበቁ ሆነው፤ ግብር ከፋዩ የወሰደውን ብድር ወይም

intangibles of the taxpayer have declined in value during the year from use in deriving business income as determined under Article25 of this Proclamation;

d) a loss on disposal of a business asset (other than trading stock) disposed of by the taxpayer during the year;

e) any other amount allowed as a deduction to the taxpayer under this Proclamation for the year.

2. Article 57 of this Proclamation and not sub-article (1) (d) of this Article shall apply to a loss on disposal of a taxable asset except when the taxable asset is a depreciable asset.

3. For the purposes of sub-article (1)(d) of this Article, a loss on disposal of a business asset is the amount by which the net book value of the asset at the time of disposal exceeds the consideration for the disposal.

**23. Interest Expenditure**

1. Subject to sub article (2) of this Article and Article 47 of this Proclamation, in

ሌላ ዕዳ ወይም ያደረገውን ስምምነት የንግድ ሥራ ገቢውን ለማግኘት ተግባር ያዋለው እንደሆነ ከዚህ ጋር በተያያዘ የተከፈለው ወለድ የግብር ከፋዩ ዓመታዊ ግብር የሚከፈልበት ገቢ በሚወሰንበት ጊዜ እንደወጪ ይያዝለታል፡፡

2. ለሚከተሉት ወጪዎች ተቀናሽ አይፈቀድም፤

ሀ/ ወለዱ በብሔራዊ ባንክ እና በንግድ ባንኮች መካከል በተደረገ ብድር ከሚታሰብ የወለድ ምጣኔ ፪% የሚበልጥ ከሆነ በተቀናሽ አይያዝም፤ ነገር ግን ወለዱ፤

1. በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ዕውቅና ለተሰጠው የፋይናንስ ተቋም የተከፈለ፤ ወይም

2. በኢትዮጵያ ለሚገኙ ሰዎች ብድር እንዲሰጥ ለተፈቀደለት የውጭ ሀገር ባንክ፤ የተከፈለ ወይም የሚከፈል ከሆነ በተቀናሽ ይያዛል፡፡

ለ/ የወለዱ ገቢ ግንኙነት ባለው ሰው የንግድ ሥራ ገቢ ውስጥ ካልተካተተ በስተቀር፣ አንድ ግብር ከፋይ በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆነ ግንኙነት ላለው ሰው የከፈለው ወይም የሚከፍለው ወለድ፤

፳፬ ለበጎ አድራጎት ዓላማ የሚደረጉ ስጦታዎች

determining the taxable income of a taxpayer for a tax year, the taxpayer shall be allowed a deduction forany interest incurred by the taxpayer in a tax year to the extent that the taxpayer has used the proceeds or benefit of the debt or other instrument or agreement that gives rise to the interest to derive business income.

2. No deduction shall be allowed for the following:

a) interestpaid or payable by a taxpayer in excess of the rate used between the National Bank of Ethiopia and commercial banks increased by 2 percentage points unless the interest is paid or payable to:

(1) a financial institution recognised by the National Bank of Ethiopia; or

(2) a foreign bank permitted to lend to persons in Ethiopia;

b) interest paid or payable by a taxpayer to a related person who is a resident of Ethiopia except when the interest is included in the business income of the related person.

**24. Charitable Donations**

1. የግብር ከፋዩ ግብር የሚከፈልበት ዓመታዊ ገቢ በሚወሰንበት ጊዜ ግብር ከፋዩ ያደረገው ስጦታ ተቀናሽ የሚደረገው ስጦታው ለሚከተሉት የተደረገ ሲሆን ነው፡-
   ሀ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ ለተመለከቱት የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፤ ወይም

መጠን ነው፡፡

ሀ/ በውጭ ሀገር የተከፈለው የገቢ ግብር፤ ወይም

ለ/ በውጭ ሀገር በተገኘው ገቢ ላይ በሠንጠረዥ "ሐ" መሠረት ተከፋይ የሚሆነው የንግድ ገቢ ግብር፣

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ለ) የተመለከተው የንግድ ገቢ ግብር የሚሰላው በዓመቱ በኢትዮጵያ ነዋሪ በሆነው ግብር ከፋይ ላይ ተፈፃሚ የሚደረገውን አማካይ የንግድ ሥራ ገቢ ግብር ምጣኔ ግብር ከፋዩ ባገኘው የተጣራ የውጭ ሀገር ገቢ ላይ ተፈፃሚ በማድረግ ነው፡፡

3. በዚህ አንቀጽ መሠረት በውጭ ሀገር የተከፈለ ግብር ሊካካስ የሚችለው

ሀ/ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነው ሰው በውጭ ሀገር ባገኘው ገቢ ላይ ሊከፍል የሚገባውን ግብር ገቢው ከተገኘበት የግብር ዘመን በኋላ ባሉት ሁለት ዓመታት ወይም ደግሞ ቢሮው በሚፈቅደው ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ የከፈለ እንደሆነ፤ እና

ለ/ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነው ሰው ግብር በውጭ አገር የታክስ ባለሥልጣን የተሰጠ ደረሰኝ ያለው እንደሆነ ብቻ ነው፡፡

4. በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነው ሰው በግብር ዓመቱ መክፈል የሚኖርበትን የንግድ ሥራ ገቢ ግብር ሲያሰላ፣ ማንኛውንም

2. The business income tax referred to in sub-article (1)(b) of this Article shall be computed by applying the average rate of business income tax applicable to the resident tax payer for the year against the net foreign income of the resident for the year.

3. A foreign tax credit shall be allowed under this Article only if:

   a) the resident taxpayer has paid the foreign income tax within 2 years after the end of the tax year in which the foreign income was derived by the taxpayer or within such further time as the Bureau allows; and

   b) the resident taxpayer has a receipt for the tax from the foreign tax authority.

4. In computing the business income tax payable by a resident taxpayer for a tax year, the taxpayer shall apply the foreign tax credit under this Article before applying any other tax credits of the taxpayer for the tax year.

5. If a foreign tax credit of a resident taxpayer for a tax year is not fully credited for the year, the excess

የግብር ማካካሻ ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት በውጭ ሀገር ለተከፈለ ግብር የተፈቀደውን ማካካሻ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

5. በአንድ የግብር ዓመት ውስጥ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነው ሰው በውጭ ሀገር የከፈለው ግብር በዚያው የግብር ዘመን ሙሉ በሙሉ የማይካካስ የሆነ እንደሆነ ሳይካካስ የቀረው ግብር ተመላሽ ሊደረግ ወይም ወደቀደመው የግብር ዓመት ሊመለስ ወይም ወደሚቀጥለው የግብር ዘመን ሊሸጋገር አይችልም፡፡

6. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም፣

ሀ) "አማካይ የንግድ ሥራ ገቢ ግብር ምጣኔ" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት ማንኛውም የግብር ማካካሻ ከመደረጉ በፊት በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነው ሰው ግብር በሚከፍልበት ገቢ ላይ ተግባራዊ የሚሆነው ምጣኔ ነው፡፡

ለ) "የውጭ ሀገር ገቢ ግብር" ማለት በከፋዩ ተቀንሶ የሚያዝን ግብር ጨምሮ በውጭ ሀገር መንግሥት ወይም በውጭ ሀገር አካባቢያዊ መንግሥት የተጣለ ግብር ሲሆን፣ ቅጣትን፣ ተጨማሪ ታክስን፣ ወይም ደግሞ ይህንን ግብር በሚመለከት የሚከፈል ወለድን አይጨምርም፡፡

ሐ) "የተጣራ የውጭ ሀገር ገቢ" ማለት በአንድ የግብር ዓመት በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነን ግብር ከፋይ በሚመለከት በዚህ ሰንጠረዥ መሠረት ግብር ከፋዩ በዓመቱ ካገኘው ጠቅላላ የውጭ ሀገር ገቢ ላይ ለግብር

credit shall not be refunded, carried back to the preceding tax year, or carried forward to the following tax year.

6. In this Article:

a) "average rate of business income tax", in relation to a resident taxpayer for a tax year, means the percentage that the business income tax payable by the taxpayer for the year, before the allowance of any tax credit under this Proclamation, is of the taxable income of the taxpayer for the year;

b) "foreign income tax" means income tax, including withholding tax, imposed by the government of a foreign country or a political subdivision of a government of a foreign country, but does not include a penalty, additional tax, or interest payable in respect of such tax; and

c) "net foreign income", in relation to a resident taxpayer for a tax year, means the total foreign income of the taxpayer for the year taxable under this Schedule, as reduced by any deductions allowed to the person under this Schedule for the year that:

ከፋዩ በዓመቱ በዚህ ሠንጠረዥ መሠረት የሚፈቀደው ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ጋር በተያያዘ ተቀናሽ የሚደረገው ወጪ ከተቀነሰ በኋላ የሚቀረው ገቢ ነው፡፡

1. የውጭ ሀገር ገቢውን ለማግኘት ሲባል ብቻ ወጪ የተደረገ እና
2. በውጭ ሀገር የሚገኝ ገቢ እራሱን የቻለ የገቢ ዓይነት ሆኖ የሚመደብ በመሆኑ የውጭ ሀገር ገቢውን ለማግኘት በወጣው መጠን በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፸፬ መሠረት የተከፋፈለ ሲሆን፣

**፵፮ የውጭ ሀገር የንግድ ሥራ ኪሳራዎች**

1. በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ግብር ከፋይ በሠንጠረዥ "ሐ" መሠረት ግብር የሚከፈልበትን የውጭ ሀገር ገቢን ለማግኘት ያወጣው ወጪ በዚህ አዋጅ መሠረት ተቀናሽ የሚደረግለት በውጭ ሀገር ካገኘው ገቢ ላይ ብቻ ነው፡፡
2. በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ግብር ከፋይ በአንድ የግብር ዓመት በውጭ ሀገር ኪሳራ ያጋጠመው እንደሆነ ኪሳራው ከደረሰበት የግብር ዘመን ቀጥሎ ላለው የግብር ዘመን የሚሸጋገር ሆኖ ይህም ኪሳራ በተሸጋገረበት የግብር ዘመን ግብር ከፋዩ በውጭ ሀገር ካገኘው ገቢ ላይ

(1) relate exclusively to the derivation of the foreign income; and

(2) are apportioned to the derivation of the foreign income in accordance with Article 74 of this Proclamation on the basis that foreign income is a separate class of income.

**46. Foreign Business Losses**

1. An amount that a resident taxpayer is allowed as a deduction under this Proclamation in deriving foreign income taxable under "Schedule C" shall be deductible only against that income.
2. If a resident taxpayer has a foreign loss for a tax year, the amount of the loss shall be carried forward to the next following tax year and allowed as a deduction in that year against the taxpayer's foreign income taxable under "Schedule C" for the following year.
3. If a resident taxpayer is not able to wholly deduct a foreign loss under sub-article (2) of this Article, the amount not deducted shall be carried forward to the next following tax year and applied as specified in sub-article (2) of this

በሠንጠረዥ "ሐ" መሠረት ተቀናሽ ይደረጋል።

3. በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነው ግብር ከፋይ ኪሳራውን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት በሙሉ ወይም በከፊል መቀነስ ያልቻለ እንደሆነ ኪሳራው በሙሉ ተቀንሶ እስከሚያልቅ ድረስ ወደ ሚቀጥሉት የግብር ዓመታት ተሸጋግሮ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት ተቀናሽ ይደረጋል። ሆኖም ግብር ከፋዩ ኪሳራው ከደረሰበት የግብር ዓመት በኋላ ካሉት አምስት የግብር ዓመታት በላይ ኪሳራውን ለማሸጋገር አይችልም።

4. ግብር ከፋዩ የውጭ ሀገር ኪሳራ ያስተናገደባቸው ሁለት ዓመታት የኖሩ እንደሆነ እና አያንዳንዱ ኪሳራ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት የተሸጋገረ እንደሆነ ግብር ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት ተጨማሪ ኪሳራዎችን ለማሸጋገር አይፈቀድለትም።

5. አንድ ግብር ከፋይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ እና ፫ የተመለከቱትን የውጭ ሃገር ኪሳራዎች ሊያሸጋግር የሚችልበት ዝርዝር የአፈፃፀም ሥርዓት የመስተዳደር ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል።

6. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም በአንድ የግብር አመት በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነን ግብር ከፋይ በሚመለከት፣ "በውጭ ሀገር

Article in that year, and so on until the loss is fully deducted, but a taxpayer shall not carry a foreign loss forward for more than five tax years after the end of year in which the loss was incurred.

4. If there has been two tax years in which a taxpayer has incurred a foreign loss and each of those losses has been carried forward under sub-article (2) of this Article, the taxpayer shall not be permitted to carry forward any further losses under sub-article (2) of this Article.

5. A taxpayer shall carry forward a foreign loss under sub-articles (2) and (3) of this Article shall be defined in the regulation to be issued by the Executive Council.

6. In this Article, "foreign loss", in relation to a resident taxpayer for a tax year, means the amount by which the deductible expenditures incurred by the taxpayer in deriving foreign income taxable under this Schedule exceeds the amount of that income for the year.

የደረሰ ኪሳራ” ማለት ግብር ከፋዩ በሠንጠረዥ "ሐ” መሠረት ግብር የሚከፈልበትን የውጭ ሀገር ገቢ ለማግኘት ያወጣቸው ወጪዎች መጠን ከጠቅላላው የውጭ ሀገር ገቢ በልጦ ሲገኝ ነው፡፡

## ፵፯ ለኩባንያ ካፒታል የሚወሰድ ብድር

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የፋይናንስ ድርጅቶችን ሳይጨምር በውጭ አገር ባለአክሲዮኖች ቁጥጥር ስር ያለና በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ አማካይ ዕዳ ከአማካይ የካፒታል መዋጮ ከ፪ ለ ፩ የበለጠ እንደሆነ ኩባንያው ለወለድ ክፍያ ያወጣው ወጪ ከዚህ በታች በተመለከተው ስሌት መሠረት በተቀናሽ እንዳይያዝለት ይደረጋል፡፡

$$ሀ \times {}^{ለ}/_{ሐ}$$

በዚህ ስሌት

ሀ/ ኩባንያው በግብር ዓመቱ ተቀናሽ እንዲደረግለት የሚጠይቀው የወለድ ወጪ፤

ለ/ ኩባንያው ከተፈቀደው መጠን በላይ የወሰደው ብድር፤ እና

ሐ/ ኩባንያው በዓመቱ ያለበት አማካይ ዕዳ፤

2. በውጭ አገር ባለአክሲዮኖች ቁጥጥር ስር ያለ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ አማካይ ዕዳ እና አማካይ የካፒታል

**47. Thin Capitalization**

1. Subject to sub-article (2) of this Article, if a foreign-controlled resident company, other than a financial institution, has an average debt to average equity ratio in excess of 2 to 1 for a tax year, a deduction shall be disallowed for the interest paid by the company during that year calculated according to the following formula:

$$\mathbf{A \times {}^{B}/_{C}}$$

where:

A is the company’s total amount of deductible interest for the year;

B is the company’s excess debt for the year; and

C is the company’s average debt for the year.

2. If the average debt to average equity ratio of a foreign-controlled resident company exceeds 2 to 1 for a tax year, sub-article (1) of this Article shall not apply if the amount of the average debt of the company for the year does not exceed the arm’s length debt amount.

3. This Article shall apply to a non-resident company with a permanent

መዋጮ በግብር ዓመቱ ከ ፪ ለ ፩ የበለጠ እንደሆነ እና የኩባንያው የግብር ዓመቱ አማካይ ዕዳ ግንኙነት ከሌላቸው ሰዎች ከተወሰደው ዕዳ የማይበልጥ ከሆነ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ከዚህ በታች በተዘረዘረው መሠረት በኢትዮጵያ በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት ባለው በኢትዮጵያ ነዋሪ ባልሆነ ኩባንያ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

ሀ/ በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት በውጭ አገር ባለአክሲዮኖች ቁጥጥር ስር ያለ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ ሆኖ ይቆጠራል፣ እና

ለ/ በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት አማካኝ ዕዳ እና አማካኝ የካፒታል መዋጮ የሚከተለውን መሠረት በማድረግ ይሰላል፡፡

1. ለዘላቂው ድርጅት የዋለው በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነው ኩባንያ የወሰደው ብድር፣ እና

2. በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነው ኩባንያ ለሥራው ማንቀሳቀሻ የመደበውና በዘላቂው ድርጅት አማካኝነት ሥራ ላይ የዋለው የካፒታል መዋጮ፣

4. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም፡-

ሀ) "ግንኙነት ከሌላቸው ሰዎች የተወሰደ ዕዳ"

establishment in Ethiopia on the basis of the following:

a) the permanent establishment is treated as a foreign-controlled resident company; and

b) the average debt to average equity ratio of the permanent establishment is calculated by reference to:

(1) the debt obligations of the non-resident company attributable to the permanent establishment; and

(2) the equity of the non-resident company attributable to the operations of the company conducted through the permanent establishment.

4. In this Article:

a) "arm's length debt amount", in relation to a foreign-controlled resident share company, means the amount of debt that a financial institution would be prepared to lend to the company in an arm's length transaction having regard to all the circumstances of the company;

ማለት በውጭ አገር ባለአክሲዮኖች ቁጥጥር ስር የሚገኝን በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ በሚመለከት አንድ የፋይናንስ ተቋም ኩባንያው የሚገኝበትን ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች መካከል በሚደረግ ግብይት አኳኋን ሊያበድረው የሚችለው ገንዘብ ነው፡፡

ለ) "አማካይ ዕዳ" ማለት በውጭ አገር ባለአክሲዮኖች ቁጥጥር ስር የሚገኝን በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ በሚመለከት በግብር ዓመቱ ውስጥ የወሰደው በሚከተለው ቀመር ስሌቱ የሚከናወን ዕዳ ነው፡፡

$$ሀ/_{12}$$

ለዚህ ስሌት አፈፃፀም፡-

ሀ- በሚቀጥለው የግብር ዓመት ውስጥ በእያንዳንዱ ወር መጨረሻ ኩባንያው የሚፈለግበት ጠቅላላ የዕዳ መጠን ነው፡ ፡

ሐ) "አማካይ የካፒታል መዋጮ" ማለት፣ በውጭ አገር ባለአክሲዮኖች ቁጥጥር ስር የሚገኝን በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ በሚመለከት፣ በግብር ዓመቱ ውስጥ የተከፈ ለ በሚከተለው ቀመር ስሌቱ የሚከናወን የካፒታል መዋጮ ነው፡፡

$$ሀ/_{12}$$

ለዚህ ስሌት አፈፃፀም፡-

b) "average debt", in relation to a foreign-controlled resident company for a tax year, is the amount calculated according to the following formula:

$$A/_{12}$$

where:

A - is the sum of the amount of debt of the company at the end of each calendar month in the tax year;

c) "average equity", in relation to a foreign-controlled resident company for a tax year, is the amount of equity calculated according to the following formula:

$$A/_{12}$$

where:

A- is the sum of the amount of equity of the company at the end of each calendar month in the tax year;

d) "debt", in relation to a foreign-controlled resident company, means the debt obligations of the company on which

ሀ- በሚቀጥለው የግብር ዓመት ውስጥ በእያንዳንዱ ወር መጨረሻ ለኩባንያው የተደረገ ጠቅላላ የካፒታል መዋጮ መጠን ነው፡፡

መ) "ዕዳ" ማለት በውጭ አገር ባለአክሲዮኖች ቁጥጥር ስር የሚገኝን በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ በሚመለከት፣ በፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች በሚወሰነው መሠረት ወለድ የሚከፈልበት የኩባንያው ዕዳ የመክፈል ግዴታ ነው፡፡

ሠ) "ዕዳ የመክፈል ግዴታ" ማለት ከቃል ኪዳን ሰነድ፣ ከሀዋላ እና ከቦንድ የሚመጣን ግዴታ ጨምሮ ለሌላ ሰው ገንዘብ መልሶ የመክፈል ግዴታ ሲሆን፣ የሚከተሉትን አይጨምርም፡፡

1. ተከፋይ ሂሳቦችን፣ ወይም
2. ወለድ የመክፈል ግዴታን የማያስከትል ማናቸውንም ገንዘብ መልሶ የመክፈል ግዴታ፣

ረ) "የካፒታል መዋጮ" ማለት በውጭ አገር ባለአክሲዮኖች ቁጥጥር ስር ያለን በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ በሚመለከት፣ የወለድ ክፍያን የማይጨምር ዕዳን መልሶ የመክፈልን ግዴታ የሚያስከትል ብድርን ጨምሮ በሂሳብ ሪፖርት ደረጃዎች መሠረት በግብር ዓመቱ ውስጥ በማናቸውም ጊዜ ተመዝግቦ የሚገኝ ከፍተኛው የኩባንያው የካፒታል መዋጮ ነው፡፡

ሰ) "የበለጠ ዕዳ" ማለት በውጭ አገር ባለአክሲዮኖች ቁጥጥር ስር ያለን

interest is payable as determined according to financial reporting standards;

e) “debt obligation” means an obligation to make a repayment of money to another person, including obligations arising under promissory notes, bills of exchange, and bonds, but not including:

a) accounts payable; or
b) an obligation to make a repayment of money in respect of which no interest is payable;

f) “equity”, in relation to a foreign-controlled resident company, means the greatest amount, at any time during a tax year, of the equity of the company as determined according to financial reporting standards and includes an obligation to make a repayment of money in respect of which no interest is payable;

g) “excess debt”, in relation to a foreign controlled resident company for a tax year, means the amount by which the company’s average debt for the year exceeds the maximum average debt allowed for the year according to the 2 to 1 ratio; and

h) “foreign-controlled resident company” means a resident company in which

በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ በሚመለከት፣ በግብር ዓመቱ ውስጥ ኩባንያው ያለበት አማካኝ ዕዳ በ፪ ለ ፩ ቀመር መሠረት ከተፈቀደለት ከፍተኛው አማካኝ ዕዳ የበለጠ ሲሆን ነው፡፡

ሸ) "በውጭ አገር ባለአክሲዮኖች ቁጥጥር ስር ያለ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ" ማለት ኩባንያው የአባልነት ጥቅም መካከል ከ፶% በላይ የሚሆነው በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ በኢትዮጵያ ነዋሪ ባልሆኑ ሰዎች ግንኙነት ካለው ወይም ካላቸው ሰዎች ጋር በመሆን የተያዘ ኩባንያ ነው፡፡

## ምዕራፍ ስድስት

## በግምት ላይ የተመሠረተ የንግድ ሥራ ግብር

### ፵፰. የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች ስለሚከፍሉት የገቢ ግብር

የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች በእያንዳንዱ የግብር ዘመን የንግድ ሥራ ገቢ ግብር የሚከፍሉት የመስተዳደር ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ በሚወሰነው የግብር በቁርጥ አከፋፈል ዘዴ ነው፡፡

## ክፍል አምስት

## ሠንጠረዥ "መ" ሌሎች ገቢዎች

### ፵፱ በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆኑ ሰዎች ገቢ

1. በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው የትርፍ ድርሻ፣ ወለድ፣ ሮያሊቲ፣ ከሥራ አመራር ክፍያ፣ የቴክኒክ አገልግሎት ክፍያ ወይም የመድን አረቦን ከኢትዮጵያ ውስጥ ያገኘ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተመለከው ምጣኔ መሠረት ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት::

more than 50% of the membership interests in the company are held by a non-resident either alone or together with a related person or persons.

## CHAPTER SIX

## PRESUMPTIVE BUSINESS TAXES

### 48. Taxation of Category 'C' Taxpayers

A Category 'C' taxpayer shall pay business income tax for each tax year in accordance with the mode of payment of tax to be determined by Regulation to be issued by the Executive Council.

## PART FIVE

## SCHEDULE 'D' –OTHER INCOME

### 49. Income of Non-residents

1. A non-resident who has derived an Ethiopian source dividend, interest, royalty, management fee, technical fee, or insurance premium shall be liable for non-resident tax at the rate specified in sub-article (2) of this Article.

2. The rate of non-resident tax is:

a) for an insurance premium or royalty , 5% of the gross amount of the premiumor royalty;

b) for a dividend or interest, 10% of the

2. በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ግብር የሚከፍልበት ምጣኔ:-

ሀ/ ለመድህን በሚከፈል አረቦን ወይም ከሮያሊቲ ጠቅላላው ክፍያ ላይ ፭% (አምስት በመቶ)፤

ለ/ ከትርፍ ድርሻ ወይም ከወለድ፣ ጠቅላላ ገቢላይ ፲% (አስር በመቶ)፤

ሐ/ ከስራ አመራር ክፍያ ወይም ከቴክኒክ አገልግሎት ክፍያ ከጠቅላላ ገቢው ላይ ፲፭% (አሥራ አምስት በመቶ).

3. የትርፍ ድርሻ፣ የወለድ፣ የሮያሊቲ፣ የስራ አመራር ክፍያ፣ የቴክኒክ አገልግሎት ክፍያ ወይም የመድን አረቦን ገቢ የተገኘው በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በቋሚነት በሚሰራ ድርጅት አማካኝነት ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚያከናውነው ሥራ የሆነ እንደሆነ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ ተፈፃሚ አይሆንም። ይህ በሚሆንበት ጊዜ እነዚህ ገቢዎች እንደሁኔታው በሰንጠረዥ "ሐ" ወይም "መ" መሠረት ግብር ይከፈልባቸዋል።

**፶. እንዲተካ በተጠየቀ የቴክኒክ አገልግሎት ክፍያ እና ሮያልቲ ላይ ስለሚከፈል ግብር**

1. ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ የሚሆነው የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ይሆናል።

ሀ/ በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በቋሚነት በሚሠራ ድርጅት አማካኝነት ሳይሆን በራሱ የቴክኒክ

gross amount of the dividend or interest; or

c) for a management or technical fee, 15 % of the gross amount of the fee.

3. Sub-article (2) of this Article shall not apply to a dividend, interest, royalty, management fee, technical fee, or insurance premium that is attributable to a business carried on by the non-resident through a permanent establishment in Ethiopia and, in that case, the amount shall be taxable under Schedule ‘C” or ‘D”, as the case may be.

**50. Taxation of Recharged Technical Fees and Royalties**

1. This Article shall apply when the following conditions are satisfied:

a) a non-resident supplies technical services or the lease of equipment other than through a permanent establishment in Ethiopia;

b) the technical services are supplied, or equipment leased, to a person (referred to as the

አገልግሎት ወይም የመሣሪያ ኪራይ(ሊዝ) አገልግሎት የሰጠ እንደሆነ፣

ለ/ የቴክኒክ አገልግሎት ወይም የመሣሪያ ኪራይ (ሊዝ) አገልግሎት የተሰጠው ("አገልግሎት ተቀባይ" ተብሎ የሚጠቀሰው) ሰው፣

1. ከኢትዮጵያ ውጪ ባለ በቋሚነት በሚሠራ ድርጅት አማካኝነት የሚሰጠውን አገልግሎት ሳይጨምር፣ በኢትዮጵያ ነዋሪ ከሆነ፣ወይም
2. በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ እናበቋሚነት በሚሠራ ድርጅት አማካኝነት የንግድ ሥራ የሚያከናውን ከሆነ፣

ሐ/ ከአቅርቦቱ ወይም ከሊዙ ጋር በተያያዘ በኢትዮጵያ ነዋሪ ላልሆነው ሰው የቴክኒክ አገልግሎት ወይም የሮያሊቲ ክፍያ የተከፈለው ከአገልግሎት ተቀባዩ ጋር ግንኙት ባለው በኢትዮጵያ ነዋሪ ባልሆነ ሰው የሆነ እንደሆነ፣

መ/ ግንኙት ያለው ሰው የቴክኒክ አገልግሎት ወይም የሮያሊቲ ክፍያውን ከአገልግሎት ተቀባዩ የጠየቀ እንደሆነ፣

2. ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ በሚሆንበት ጊዜ ግንኙነት ያለው ሰው ለአገልግሎቱ ተቀባይ የቴክኒክ አገልግሎቱን ወይም የመሣሪያውን ሊዝ አገልግሎት እንደሰጠ ተቆጥሮ እንዲሁም እንዲተካ የተጠየቀው ገንዘብ ለቴክኒክ

"recipient") who is:

(1) a resident of Ethiopia, other than in relation to a business conducted by the resident through a permanent establishment outside Ethiopia; or

(2) a non-resident conducting business in Ethiopia through a permanent establishment;

c) the technical fee or royalty in respect of the supply or lease is paid to the non-resident by another non-resident that is a related person of the recipient;

d) the technical fee or royalty is recharged by the related person to the recipient.

2. If this Article applies, the Proclamation shall apply as if the related person is supplying the technical services or leased equipment to the recipient and the recharged amount is the technical fee for the services or royalty for the leased equipment.

**51. Taxation of Non-resident Entertainers**

1. A non-resident entertainer or group of non-resident entertainers who has derived

አገልግሎቱ ወይም ለመሣሪያው ሊዝ የተከፈለ ክፍያ እንደሆነ ተቆጥሮ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

**፶፩ በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆኑ የመዝናኛ አገልግሎት ሰጪዎች ግብር**

1. በኢትዮጵያ በሚካሄድ የመዝናኛ አገልግሎት ተግባር ላይ ተሳታፊ የሚሆን በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ የመዝናኛ አገልግሎት የሚሰጥ ሰው ወይም ቡድን ከመዝናኛ አገልግሎት በሚያገኘው ጠቅላላ ገቢ ላይ ፲% ግብር ይከፍላል፡፡
2. በቡድን አባልነት የሚገኝን ገቢ ጨምሮ ከመዝናኛ አገልግሎት የሚገኘው ገቢ ተጠቃሚ አዝናኙ ሳይሆን ሌላ ሰው የሆነ እንደሆነ ይህ ሰው በሚያገኘው ጠቅላላ ገቢ ላይ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
3. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም፡-
   ሀ) የመዝናኛ አገልግሎት ሰጪ" ስፖርተኛን እና ሙዚቀኛን ይጨምራል፤
   ለ) ቡድን" የስፖርት ክለብን (ቡድንን) ይጨምራል፤
   ሐ) የመዝናኛ አገልግሎት" የስፖርት ውድድርን ይጨምራል፡፡

**፶፪ ሮያሊቲ**

1. በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው ሮያሊቲ ያገኘ እንደሆነ በጠቅላላ የሮያሊቲ ክፍያ ላይ ፭% (አምስት በመቶ) የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

income from the participation by the entertainer or group in a performance-taking place in Ethiopia shall be liable for income tax at the rate of 10% on the gross income derived from the performance.

2. When the income for a performance by an entertainer, including as member of a group, is derived not by the entertainer but by another person, sub-article (1) of this Article shall apply to the gross income derived by that other person.
3. In this Article:
   a) “entertainer” includes musician and sportsperson;
   b) “group” includes a sporting team; and
   c) “performance” includes a sporting event.

**52. Royalties**

1. A resident of Ethiopia who derives a royalty shall be liable for income tax at the rate of 5% on the gross amount of the royalty.
2. A non-resident who derives an Ethiopian source royalty that is attributable to a permanent establishment of the non-resident in Ethiopia shall be liable for income tax at the rate of 5% on the gross amount of the royalty.

2. በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው ቋሚ ድርጅቱ አማካይነት በኢትዮጵያ ውስጥ ሮያሊቲ ገቢ ሲያገኝ በጠቅላላ የሮያልቲ ክፍያ ላይ ፭% (አምስት በመቶ) የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

**፶፫ የትርፍ ድርሻ**

1. በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነና የትርፍ ድርሻ ያገኘ ሰው በጠቅላላው የትርፍ ድርሻ ገቢ ላይ ፲% (አስር በመቶ) የትርፍ ድርሻ የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡
2. በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው በቋሚነት በሚሠራ ድርጅት አማካይነት በኢትዮጵያ ውስጥ ትርፍ ድርሻ ገቢ ሲያገኝ በጠቅላላ የትርፍ ገቢው ላይ ፲% (አስር በመቶ) የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

**፶፬ ወለድ**

1. በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነና ወለድ ያገኘ ሰው፡-

ሀ/ ወለዱን ያገኘው በገንዘብ ተቋማት ገንዘቡን በቁጠባ አስቀምጦ ሲሆን በጠቅላላው የወለድ ገቢ ላይ ፭% (አምስት በመቶ) የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

ለ/ በሌላ በማንኛውም ሁኔታ ወለድ የሚያገኝ

**53. Dividends**

1. A resident of Ethiopia who derives a dividend shall be liable for income tax at the rate of 10% of the gross amount of the dividend.

2. A non-resident who derives an Ethiopian source dividend that is attributable to a permanent establishment of the non-resident in Ethiopia shall be liable for income tax at the rate of 10% on the gross amount of the dividend.

**54. Interest**

1. A resident of Ethiopia who derives interest shall be liable for income tax at the rate of:

a) in the case a savings deposit with a financial institution that is a resident of Ethiopia, 5% of the gross amount of the interest; or

b) in any other case, 10% of the gross amount of the interest.

2. A non-resident who derives Ethiopian source interest that is attributable to a permanent establishment of the non-resident in Ethiopia shall be liable for income tax at the rate of:

ከሆነ በጠቅላላው የወለድ ገቢ ላይ ፲% (አስር በመቶ) የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

2. በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው ቋሚ ድርጅቱ አማካይነት በኢትዮጵያ ውስጥ የወለድ ገቢ ሲያገኝ፡-

ሀ/ ወለዱን ያገኘው በኢትዮጵያ ነዋሪ በሆነ የገንዘብ ተቋም ገንዘቡን በቁጠባ አስቀምጦ ሲሆን በጠቅላላው የወለድ ገቢ ላይ ፭% (አምስት በመቶ) የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

ለ/ በሌላ በማንኛውም ሁኔታ ወለዱን የሚያገኝ ከሆነ በጠቅላላው የወለድ ገቢ ላይ ፲% (አስር በመቶ) የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

3. በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በማንኛውም ሁኔታ የወለድ ገቢ የሚያገኝ ከሆነ በጠቅላላው የወለድ ገቢ ላይ ፲% (አስር በመቶ) የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

**፶፭ ከዕድል ሙከራ የሚገኝ ገቢ**

1. በኢትዮጵያ ውስጥ በሚደረጉ የዕድል ሙከራዎች ተሳትፎ ገቢ ያገኘ ሰው ባሸነፈው ጠቅላላ ገቢ ላይ ፲፭% (አስራ አምስት በመቶ) የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)

a) in the case a savings deposit with a financial institution that is a resident of Ethiopia, 5% of the gross amount of the interest; or

b) in any other case, 10% of the gross amount of the interest.

3. A non-resident, for interest derived in every case, shall be liable for income tax at the rate of 10% on the gross amount of interest income.

**55. Income from Games of Chance**

1. A person who derives income from winning at games of chance held in Ethiopia shall be liable for income tax at the rate of 15% on the gross amount of the winnings.

2. In computing the gross amount of winnings under sub-article (1) of this Article, no deduction shall be allowed for any loss incurred by the person from games of chance.

3. Sub-article (1) of this Article shall not apply when the winnings are less than 1000 Birr.

4. In this Article, “games of chance” means a game whose outcome

መሠረት በዕድል ሙከራ አሸናፊነት የተገኘው ገቢ ሲሰላ ገቢውን ያገኘው ሰው የዕድል ሙከራውን ሲያከናውን የደረሰበት ኪሳራ ተቀናሽ አይደረግለትም፡፡

3. በዕድል ሙከራ የተገኘው ገንዘብ ከ፩፻ ብር (አንድ ሺህ ብር) በታች ሲሆን የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

4. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም "የዕድል ሙከራ" ማለት የጨዋታው ውጤት በተሳታፊው ችሎታ ሳይሆን በዋነኝነት በዕድል ላይ የተመሰረተ ሲሆን፣ ሎተሪን፣ የካርታ ጨዋታንና ቶምቦላንም ይጨምራል፡፡

## ፶፮ ሀብትን አልፎ አልፎ በማከራየት የሚገኝ ገቢ

1. በኢትዮጵያ ውስጥ አልፎ አልፎ ሀብት (ማንኛውንም መሬት፣ ቤት፣ ወይም የሚንቀሳቀስ ንብረት) በማከራየት ገቢ የሚያገኝ ሰው ከጠቅላላው የኪራይ ገቢ ላይ ፲፭% (አስራ አምስት በመቶ) የኪራይ ገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፵፱ ወይም ፶፪ መሠረት የሮያሊቲ ግብር በሚከፈልበት ገቢ ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

## ፶፯ የካፒታል ሀብቶችን በማስተላለፍ የሚገኝ ጥቅም

1. አንድ ሰው "ግብር የሚከፈልበት ሀብት" ተብሎ የሚጠቀስን የማይንቀሳቀስ ሀብት፣

depends primarily on chance rather than the skill of the participant, including a lottery or tombola.

## 56. Income from Casual Rentals

1. A person who derives income from the casual rental of property in Ethiopia (including any land, building, or movable property) shall be liable for income tax on the annual gross rental income at the rate of 15% of the gross amount of the rental income.

2. This Article shall not apply to income that is a royalty taxable under Article 49 or 52 of this Proclamation.

## 57. Gains on Disposal of Capital Assets

1. A person who derives a gain on the disposal of immovable property, a share, or bond (referred to as a "taxable asset') shall be liable to pay income tax at the rate specified in sub-article (2) of this Article on the amount of the gain.

2. The rate of income tax under sub-article (1) of this Article shall be:

a) for a class 'A' taxable asset, 15%;

b) for a class 'B' taxable asset, 30%.

አክሲዮን ወይም ቦንድ በማስተላለፍ ጥቅም ያገኘ እንደሆነ በተገኘው ጥቅም ላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተመለከተው ምጣኔ መሠረት የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በሚከፈለው ግብር ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው ምጣኔ፣

ሀ/ለምድብ "ሀ" ግብር የሚከፈልባቸው ሀብቶች ፲፭% (አሥራ አምስት በመቶ)፤

ለ/ለምድብ "ለ" ግብር የሚከፈልባቸው ሀብቶች ፴% (ሠላሳ በመቶ) ይሆናል፡፡

3. ግብር የሚከፈልበትን ሀብት በማስተላለፍ የሚገኘው ጥቅም ሀብቱን በማስተላለፍ ከተገኘው ዋጋ ሀብቱ በተላለፈበት ጊዜ ከነበረው ዋጋ በልጦ የተገኘው የገንዘብ መጠን ነው፡፡

4. በዚህ ንዑስ አንቀጽ የተዘረዘሩት እንደተጠበቁ ሆኖ፣ አንድ ሰው በግብር ዓመቱ ውስጥ አንድን ግብር የሚከፈልበት ሀብት ሲያስተላለፍ ኪሳራ የደረሰበት እንደሆነ ኪሣራው በዚያው የግብር ዓመት በተመሳሳይ ምድብ ያለ ግብር የሚከፈልበት ሀብት ሲሸጥ ከሚገኘው ገቢ ጋር እንዲቻቻል ይደረጋል፡፡

ሀ/ ኪሳራው የሚውለው በዚህ አንቀጽ መሠረት የተገኘን ገቢ ለማቻቻል ነው፡፡

3. The amount of a gain on disposal of a taxable asset by a person shall be the amount by which the consideration for the disposal of the asset exceeds the cost of the asset at the time of disposal.

4. If a person makes a loss on disposal of a taxable asset during a tax year, the loss shall be recognised and be available to offset a gain on disposal of a taxable asset of the same class during the year subject to the following:

a) the loss may be used only to offset gains under this Article;

b) the unused amount of a loss can be carried forward indefinitely for offset against gains on disposal of taxable assets of the same class until fully offset;

c) no loss is recognised on the disposal of a taxable asset by a person to a related person;

d) the person has substantiated the amount of the loss to the satisfaction of the Bureau.

ለ/ ያልተቻቻለው ኪሳራ ተቻችሎ እስከሚያልቅ ድረስ በተመሳሳይ ምድብ ውስጥ ያለ ንብረት በሚሸጥበት ጊዜ ለማካካስ እንዲውል ላልተወሰነ ጊዜ ይሸጋገራል፡፡

ሐ/ አንድ ሰው ግንኙነት ላለው ሰው ሀብት ያስተላለፈ እንደሆነ የደረሰው ኪሳራ ዕውቅና አይሰጠውም፡፡

መ/ አንድ ሰው የደረሰበትን ኪሳራ ቢሮውን በሚያሳምን መንገድ ማስረዳት የቻለ እንደሆነ ነው፡፡

5. ግብር የሚከፈልበትን ሀብት በማስተላለፍ የደረሰው ኪሳራ ሀብቱ በተሸጠበት ጊዜ ለሀብቱ የወጣው ወጪ ሀብቱ ከተላለፈበት ዋጋ የሚበልጠው የገንዘብ መጠን ነው፡፡

6. የተላለፈው ግብር የሚከፈልበት ሀብት የንግድ ሀብት በሚሆንበት ጊዜ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፭ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

7. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም

ሀ/ **"የማይንቀሳቀስ ሀብት"** ለመኖሪያ አገልግሎት የተገነባ ህንጻ ከመተላለፉ በፊት ለመኖሪያነት ያገለገለ ወይም ያላገለገለ ወይም መዋቅራዊ ፕላኑ ለመኖሪያ ሆኖ የተገነባው ጅምር ህንጻ የሚሰጠው አገልግሎት የማይታወቅን ህንጻ አይጨምርም፡፡

ለ/ “ምድብ "ሀ” ግብር የሚከፈልበት ሃብት”

5. The amount of a loss on disposal of a taxable asset is the amount by which the cost of the asset at the time of disposal exceeds the consideration for the disposal.

6. Article 35 of this Proclamation shall apply when the taxable asset transferred is also a business asset.

7. In this Article:

a) “immovable property” shall not include a building held and wholly used as a private residence for 2 years prior to the disposal of the property;

b) “Class ‘A’ taxable asset” means immovable property; and

c) “Class ‘B’ taxable asset” means shares and bonds.

d) Subject to the provision of sub-paragraph (2) of article 2 of this proclamation, the structural plan does not include a house that has been used as a residence for more than one year from the date of closing the business.

ማለት የማይንቀሳቀስ ንብረት ማለት ነው፡፡

ሐ/ “ምድብ "ለ” ግብር የሚከፈልበት ሃብት” ማለት አክሲዮኖችና ቦንዶች ማለት ነው፡፡

መ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (2) በፊደል ተራ (ሀ) የተደነገገው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ መዋቅራዊ ፕላኑ ለመኖሪያ ቤት ሆኖ ለንግድ ሥራ ሲያገለግል የቆየ ህንጻ ድርጅቱን ከዘጋበት ቀን ጀምሮ ከአንድ ዓመት በላይ ለመኖሪያ ያገለገለ ቤትን አይጨምርም፡፡

**፶፰ ንፋስ አመጣሽ ገቢ**

1. የፋይናንስ ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ ከተመለከቱ የንግድ ሥራዎች የሚገኝ ንፋስ አመጣሽ ገቢ በመመሪያው በተመለከተው የማስከፈያ ልክ ግብር ይከፈልበታል፡፡

2. የፋይናንስ ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ፡-

ሀ/ ንፋስ አመጣሽ ገቢ ነው ሊባል የሚችለው የገቢ መጠን፣

ለ/ በንፋስ አመጣሽ ገቢ ላይ የተጣለውን ግብር ሊከፍሉ የሚገባቸውን የንግድ ሥራዎች ዓይነት፣

ሐ/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚከፈለው ግብር ሥራ ላይ የሚውልበትን ቀን፣

**58. Windfall Profit**

1. Windfall profit obtained from businesses prescribed in a directive to be issued by the Bureau shall be liable to tax at a rate to be determined in such Directive.
2. The Bureau is empowered to prescribe by a directive
   a) the amount of income to be considered as windfall profit;
   b) businesses that are subject to tax levied on windfall profit;
   c) the date on which such tax shall become effective;
   d) the manner in which the tax is assessed and factors that need to be taken into consideration;
3. The Finance Bureau may, taking into consideration the nature of the business, prescribe different amounts to be considered as windfall profit and rates for different types of businesses.
4. In this Article, “windfall profit” means any unearned, unexpected, or other non-recurring gain.

መ/ የግብር አወሳሰኑን ዘዴ እና ለግብሩ አወሳሰን መሠረት የሚሆኑ ታሳቢዎችን፣ እንዲወስን ስልጣን ተሰጥቶታል።

3. የፋይናንስ ቢሮ የንግድ ሥራ ባህሪያትን ከግምት ውስጥ በማስገባት ለተለያዩ የንግድ ሥራዎች ንፋስ አመጣሽ ገቢ የሚባለው የገንዘብ መጠን እንዲለያይ ለማድረግ እንዲሁም የተለያየ የግብር ማስከፈያ ልክ ለመወሰን ይችላል።

4. በዚህ አንቀጽ "ንፋስ አመጣሽ ገቢ" ማለት ማንኛውም ያለልፋት የሚገኝ፣ ያልተጠበቀ ወይም ሌላ ተደጋግሞ የማይገኝ ገቢ ነው።

**፶፱ ያልተከፋፈለ ትርፍ**

የፋይናንስ ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በአንድ የግብር ዓመት ግብር ከተከፈለ በኋላ ለአባላቱ ያልተከፋፈለ እና መልሶ ኢንቨስት ያልተደረገ የተጣራ የድርጅቱ ትርፍ ፲% (አሥር በመቶ) ግብር ይከፈልበታል።

**፷ በቋሚነት በሚሠራ ድርጅት የሚላክ ትርፍ**

፩ በኢትዮጵያ ውስጥ በቋሚነት በሚሠራ ድርጅት አማካኝነት የንግድ ሥራ የሚያከናውን በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ ካለው በቋሚነት በሚሠራ ድርጅት በሚላክለት ትርፍ ላይ ፲% (አሥር በመቶ) ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት።

፪ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አፈጻጸም

**59. Undistributed profit**

Tax shall be paid at the rate of 10% on the net undistributed profit of a body in a tax year to the extent that it is not reinvested, in accordance with the directive to be issued by the Finance Bureau.

**60. Repatriated Profit**

1. A non-resident body conducting business in Ethiopia through a permanent establishment shall be liable for tax at the rate of 10% on the repatriated profit of the permanent establishment.
2. The mode of application of sub article (1) of this Article shall be determined by the regulations to be issued by the Executive council.

**61. Other Income**

A person who derives any incomethat is not taxable under Schedule A, B, C, or the other Articles of this Schedule shall be liable for income tax at the rate of 15% on the gross amount of the income.

**62. General Provisions Relating to Schedule 'D' Income**

1. Tax under Schedule D shall not apply to:

a) an amount that is liable to tax under another Schedule; or

የሚመራው የመስተዳደር ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሠረት ይሆናል፡፡

**፷፩ ሌሎች ገቢዎች**

በሠንጠረዥ "ሀ"፣ "ለ"፣ "ሐ" እና በዚህ ሠንጠረዥ ሌሎች አንቀጾች መሠረት የገቢ ግብር የማይከፈልበት ማንኛውንም ገቢ ያገኘ ሰው በጠቅላላ ገቢው ላይ ፲፭% (አሥራ አምስት በመቶ) የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል፡፡

**፷፪ ከሠንጠረዥ "መ" ጋር የተያያዙ ጠቅላላ ድንጋጌዎች**

1. በሠንጠረዥ "መ" መሠረት የሚጣል ግብር፤

ሀ/ በሌሎች ሠንጠረዦች ሥር ግብር ለሚከፈልበት ገቢ ተፈጻሚ አይሆንም፤ ወይም

ለ/ ከገቢ ግብር ነፃ በሆኑ ገቢዎች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

2. በዚህ ሠንጠረዥ መሠረት የሚጣለው ግብር በገቢው ላይ የመጨረሻ ግብር ይሆናል፡፡

3. በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው ያገኘው የሮያሊቲ፣ የትርፍ ድርሻ፣ የወለድ ወይም በአንቀጽ ፷፩ የተመለከተውን ግብር የሚከፈልበትን ሀብት በመሸጥ ያገኘው ገቢ ከውጭ ሀገር የተገኘ እንደሆነ፣ ይህ ሰው በዚህ ሠንጠረዥ ከሚከፈለው ገቢ ላይ በውጭ ሀገር በዚሁ ገቢ ላይ የከፈለው ግብር ከዜሮ በታች ሳይወርድ ተቀናሽ እንዲደረግ ይፈቀድለታል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ተቀናሽ ያልተደረገን ግብር ለማሸጋገር

b) an amount that is exempt income.

2. Tax imposed on income under this Scheduleshall be a final tax on the income.

3. If a royalty, dividend, interest, gain on disposal of a taxable asset, or income referred to in Article 61of this Proclamation derived by a resident of Ethiopia is foreign income, the resident is allowed to reduce, but not below zero, the tax payable under this Schedule in respect of the income by the amount of any foreign tax paid in respect of the income.

4. There shall be no carry forward of any unreduced tax under sub-article (3) of this Article.

5. The liability of a person for income tax under Article 49, 50, 51, 52, 53,54 or 55 of this Proclamation shall be discharged if awithholding agent has withheld tax from the income in accordance with Part Ten of this Proclamation.

## PART SIX

## SCHEDULE 'E' – EXEMPT INCOME

**63. Exempt Income**

1. The following amounts are exempt income for the purposes of this Proclamation:

a) Subject to the limits set forth in the directive to be issued by the Bureau

አይቻልም፡፡

5. ግብርን ቀንሶ የመያዝ ኃላፊነት ያለበት ሰው በዚህ አዋጅ ክፍል አስር መሠረት ግብሩን ቀንሶ ያስቀረ እንደሆነ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፱፣ ፶፣ ፶፩፣ ፶፪፣ ፶፫፣ ፶፬ ወይም ፶፮ በተመለከተው መሠረት ግብር ከፋዩ ያለበትን ግብር የመክፈል ግዴታ እንደተወጣ ይቆጠራል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ሠንጠረዥ “ሠ” - ከገቢ ግብር ነጻ የሆነ ገቢ

### ፷፫ ከገቢ ግብር ነፃ የሆነ ገቢ

1. ለዚህ አዋጅ አፈጻፀም ሲባል የሚከተሉት ገቢዎች ከገቢ ግብር ነጻ ናቸው፡

ሀ/ የፋይናንስ ቢሮ በዚህ ፊደል በተራ ቁጥር (፪)፣ (፫)፣ (፬) እና (፮) በተመለከቱት ላይ በሚያወጣው መመሪያ የሚያደርገው ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለተቀጣሪው የሚከፈሉ የሚከተሉት ገቢዎች ከገቢ ግብር ነፃ ናቸው፡፡

1. ሠራተኛው ሲታመም አሠሪው ለሠራተኛው ህክምና አገልግሎት የከፈለለት ገንዘብ፤
2. በሥራ ውል መሠረት ለሠራተኛው የሚከፈል የትራንስፖርት አበል፤
3. በሥራ ቦታው ወይም በሥራ ሁኔታው አስቸጋሪነት ምክንያት ለሠራተኛው የሚከፈል አበል፤
4. ሠራተኛው ከመደበኛ ሥራው

in regard to items specified under number (2), (3), (4) and (6)of this paragraph following benefits provided to an employee:

(1) an amount paid by an employer to cover the actual cost of medical treatment of an employee;

(2) an allowance to be paid for a means of transportation granted under a contract of employment;

(3) a hardship allowance;

(4) transport expenses and per diem payments to an employee travelling on a tour of duty;

(5) travelling expenses paid to an employee recruited from place other than the place of employment on joining or completion of employment, including, in the case of a foreign employee, travel expenses from and to their country of origin, but only if the travel expenses have been paid pursuant to specific provisions of the employee’s contract of employment;

(6) food and beverages provided for free to an employee by an employer conducting a mining, manufacturing, or agricultural business;

ውጪ ሥራውን ለማከናወን ሲንቀሳቀስ የሚከፈለው የመጓጓዣ ወጪ እና የውሎ አበል፤

5. የመጓጓዣ ወጪው በቅጥሩ ውሉ መሠረት የተከፈለ ከሆነ ከሥራ ቦታው ውጪ ተመልምሎ ለተቀጠረ ሠራተኛ ወደ ሥራው ሲመጣ ወይም ሥራውን አጠናቆ ሲመለስ የሚከፈለው የመጓጓዣ ወጪ፣ እንዲሁም የውጭ ሀገር ሠራተኞች ከሀገራቸው ሲመጡና ወደ ሀገራቸው ሲመለሱ የሚከፈል የመጓጓዣ ወጪ፤

6. የማዕድን ማውጣት፣ የማኑፋክቸሪንግ እና የግብርና ሥራ የሚሠራ ቀጣሪ ለተቀጣሪው በነፃ የሚያቀርበው ምግብና መጠጥ፤

7. የኢትዮጵያ መንግሥት በውጭ አገር ለሚመድባቸው ሠራተኞች የሚከፈል አበል፤

ለ/ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ወይም የመንግሥት መስሪያ ቤቶች የቦርድ አባል ወይም ፀሐፊ በመሆን የሚከፈል አበል፡፡

ሐ/ ለሠራተኛው ጥቅም ተብሎ ከተቀጣሪው የወር ደመውዝ ፲፭% (አሥራ አምስት በመቶ) ባልበለጠ መጠን በየወሩ በቀጣሪው የሚዋጣ የጡረታ መዋጮ ወይም የፕሮቪደንት ፈንድ፡፡

(7) allowances paid by the Ethiopian government to employees engaged in public service in a foreign country

b) allowances paid to members and secretaries of boards of public enterprises or public bodies;

c) contributions by an employer to a pension or a provident fund for the benefit of an employee provided the monthly total of contributions does not exceed 15% of the monthly employment income of the employee;

d) a pension to the extent exempt from tax under the Public Servants Pension Proclamation No.714/2019 with amendment or the Private Organization Employees' Pension Proclamation No.715/2019 with amendment;

e) an amount derived by the Regional Government from activities that are incidental to official operations;

f) an amount exempt from tax to the extent provided for under an international agreement;

g) an amount exempt from tax to the extent provided for under a provision (referred to as an “exemption provision”) in an agreement entered into by the Government of Ethiopia when the following conditions are satisfied:

መ/ በመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ ቁ. ፩ሺ፱፻፺፯/፪ሺ፲፩ እና በግል ድርጅት ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ ቁ. ፩ሺ፱፻፺፰/፪ሺ፲፩ ከግብር ነፃ የተደረገ የጡረታ ገቢ፤

ሠ/ የክልል መንግሥታት ከመደበኛ ሥራዎቻቸው ጋር በተያያዘ የሚያገኙት ገቢ፤

ረ/ በዓለም ዐቀፍ ስምምነት መሠረት ከግብር ነጻ የሆነ የገቢ መጠን፤

ሰ/ በኢትዮጵያ መንግሥት በተደረገ ስምምነት (ከዚህ በኋላ "ከግብር ነፃ ማድረግ የሚያስችል አንቀጽ” ተብሎ የሚጠቀስ) መሠረት ማናቸውም ገቢ ከግብር ነፃ የሚሆነው የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ነው፡፡

1. ስምምነቱ የተደረገው ለመንግሥት የገንዘብ፣ የቴክኒክ፣ ሰብአዊ ወይም አስተዳደራዊ እርዳታ ለማቅረብ የሆነ እንደሆነ፤
2. ከግብር ነፃ ማድረግ የሚያስችለውን አንቀጽ በሚመለከት የፋይናንስ ቢሮ መስማማቱን በጽሑፍ ሲገልጽ፤

ሸ/ በማንኛውም መስክ ለላቀ የሥራ ክንውን ወይም በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር_______/2016-አንቀጽ መሠረት የሚሰጥ ሽልማት፤

(1) the agreement is for the provision of financial, technical, humanitarian, or administrative assistance to the Government; and

(2) the Bureau has concurred, in writing, with the exemption provision;

h) a public award for outstanding performance in any field or an award granted under Article ……./2024 of the Tax Administration Proclamation;

i) an amount as compensation for personal injury or the death of another person;

j) subject to Article 57 of this proclamation, a cash amount, or the value of property, acquired by gift or inheritance, other than a gift that is employment, rental or business income;

k) a scholarship or bursary for attendance at an educational institution;

l) maintenance or child support payments;

m) the income of a non-profit organisation other than business income that is not directly related to the core function of the

ቀ/ በተቀባዩ ላይ በደረሰ ጉዳት ወይም በሌላ ሰው ሞት ምክንያት የሚከፈል ካሳ፤

በ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፯ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ስጦታው የመቀጠር፣የኪራይ ወይም የንግድ ገቢ ካልሆነ በስተቀር በስጦታ ወይም በውርስ የሚገኝ ጥሬ ገንዘብ ወይም ንብረት፤

ቨ/ በትምህርት ተቋም ውስጥ ትምህርትን በነጻ ለመከታተል የሚፈጸም ክፍያ፤

ተ/ ለቀለብ ወይም ለህጻናት ድጋፍ የሚሰጡ ክፍያዎች፤

ቸ/ ድርጅቱ ከተቋቋመበት ዓላማ ጋር የማይገናኝ የንግድ ገቢን ሳይጨምር ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት የሚያገኘው ገቢ፣

ኀ/ ገንዘብ በሚቆጠርበት ጊዜ ለሚደርሰው ጉድለት ማካካሻ በሚሆን መጠን ብቻ ቀጣሪው ለተቀጣሪው የሚከፍለው እና ለዚሁ ዓላማ መዋሉ የተረጋገጠ የጥሬ ገንዘብ ማካካሻ ክፍያ፣

ነ/ በሌላ ሕግ መሠረት በተለይ ከገቢ ግብር ነጻ የተደረገ ገቢ፣

ኘ/ ለመኖሪያ ቤት ሠራተኞች የሚከፈል ደመወዝ፤

2. የመስተዳደር ምክር ቤት በሚያወጣው

organisation;

n) a cash indemnity allowance paid byan employer to an employee, but only to the extent that the allowance compensates the employee for shortfalls on money counts;

o) an amount that is specifically exempted from income tax under another law;

p) salaries paid to domestic servants;

2. The Executive Council may, by regulations, exempt any income for economic, administrative, or social reasons.

## PART SEVEN

## COMMON PROVISIONS

## CHAPTER ONE

## ASSETS

### 64. Acquisition of an Asset

A person acquires an asset when legal title to the asset passes to the person, including, in the case of an asset that is a right or option, the granting of the right or option to the person.

### 65. Disposal of an Asset

1. A person disposes of an asset when the person has sold, exchanged, or otherwise transferred legal title to

ደንብ ለኢኮኖሚ፣ ለአስተዳደራዊ ወይም ለማህበራዊ ምክንያቶች አንድን ገቢ ከገቢ ግብር ነጻ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ክፍል ሰባት
## የወል ድንጋጌዎች

### ምዕራፍ አንድ
### ሀብት

**፰፬ ሀብት ስለማግኘት**

አንድ ሰው ሀብት አገኘ የሚባለው ሕጋዊ የሀብት ባለቤትነት ስም ከተላለፈለት ጊዜ አንስቶ ሲሆን ሀብቱ መብት ወይም ምርጫ በሚሆንበት ጊዜ ይህ መብት ወይም ምርጫ የተሰጠበትንም ጊዜ ይጨምራል፡፡

**፰፭ ሀብትን ስለማስተላለፍ**

1. አንድ ሰው ሀብቱን አስተላለፈ የሚባለው ይህ ሰው ሀብቱን ሲሸጥ፣ ሲለውጥ ወይም በሌላ መንገድ በሀብቱ ላይ ያለውን የባለቤትነት ስም ሲያስተላልፍ ሲሆን፣ ሀብቱ እንዲሠረዝ፣ ለቀድሞ ባለቤቱ እንዲመለስ፣ እንዲጠፋ፣ እንዲወድም፣ ጊዜው እንዲያልፍ ወይም ለሌላ ተላልፎ እንዲሠጥ ማድረግን ይጨምራል፡፡
2. ማናቸውም ሰው ከዚህ ቀደም ያልነበረ ሀብት የሌላ ሰው ሀብት እንዲሆን ያደረገ እንደሆነ፣ ይህንን ያደረገው ሰው ሀብቱ በተፈጠረበት ጊዜ በባለቤትነቱ ስም የነበረን ሀብት ለሁለተኛው ሰው እንዳስተላለፈ ይቆጠራል፡፡
3. አንድ ሀብት በውርስ ወይም በኑዛዜ ከተላለፈ፣ ሀብቱ በተላለፈበት ጊዜ ሟቹ ሀብቱን እንዳስተላለፈ ይቆጠራል፡፡

the asset, and includes when the asset iscancelled, redeemed, relinquished, destroyed, lost, expired, or surrendered.

2. If a person creates an asset in another person being an asset that did not previously exist, the first-mentioned person shall be treated as having made a disposal of the asset to the second-mentioned person at the time the asset is created.
3. If an asset is transmitted by succession or under a will, the deceased shall be treated as having disposed of the asset at the time the asset is transmitted.
4. A disposal or change shall include the disposal of a part of an asset.
5. The vesting of an asset of a person (referred to as the “owner”) in a liquidator, trustee-in-bankruptcy, or receiver shall not be treated as a disposal of the asset for the purposes of this Proclamation, and acts done in relation to the asset by the liquidator, trustee-in-bankruptcy, or receiver shall be treated as done by the owner.

4. ሀብትን ማስተላለፍ የአንድን የንግድ ሀብት የተወሰነ ክፍል መሸጥ ወይም መለወጥንም ይጨምራል፡፡

5. ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የአንድን ሰው ሀብት ("ባለቤቱ” ተብሎ የሚጠቀስ) ለአጣሪ፣ በኪሣራ ሂደት ለተሰየመ ባለአደራ፣ ወይም ለተቀባይ መስጠት ንብረቱን እንደመሸጥ ወይም መለወጥ የማይቆጠር ሲሆን ከሀብቱ ጋር ተያይዞ በአጣሪው፣ በባለአደራው ወይም በተቀባዩ የሚከናወኑ ተግባራት ባለቤቱ እንዳከናወናቸው ይቆጠራሉ፡፡

**፷፮ ለሀብት የሚደረግ ወጪ**

1. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ የአንድ ሀብት (ግዙፋዊ ህልዎት የሌላቸው የንግድ ሥራ ሀብቶችን ሳይጨምር) ወጪ የሚከተሉት ድምር ይሆናል፣

   ሀ/ ሀብቱ በተገኘበት ጊዜ በዓይነት የሚሰጥን ሀብት ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ጨምሮ፣ ባለሀብቱ ለሀብቱ የከፈለው ዋጋ ሲሆን ሀብቱ የተገነባ፣ የተመረተ፣ ወይም የለማ እንደሆነ ለግንባታ፣ ለማምረት ወይም ለማልማት የወጣውን ወጪ ይጨምራል፡፡

   ለ/ ሀብቱን በማግኘት፣ በመሸጥ ወይም በመለወጥ ሂደት የወጣ ማንኛውም ወጪ፤

**66. Cost of an Asset**

1. Subject to this Article, the cost of an asset (other than a business intangible) of a person shall be the total of the following amounts:

a) the total consideration given by the person for the asset, including the fair market value of any consideration in kind determined at the time the asset is acquired and, if the asset is constructed, produced, or developed, the cost of construction, production, or development;

b) any incidental expenditure incurred by the person in acquiring or disposing of the asset;

c) any expenditure incurred by the person to install, alter, renew, reconstruct, or improve the asset.

2. Subject to this Article, the cost of a business intangible is:

a) in relation to a business intangible referred to in paragraph (1), (2), or (3) of the definition of “business intangible” in sub article (7) (a) of Article 25 of this Proclamation, the total expenditure incurred by the person in acquiring, creating, improving, and renewing the intangible, and any incidental expenditure incurred in acquiring or disposing of the intangible; or

ሐ/ ሀብቱ ለመትከል፣ ለመቀየር፣ ለማደስ፣ መልሶ ለመገንባት ወይም ለማሻሻል ባለሀብቱ ያወጣው ማንኛውም ወጪ፤

2. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የአንድ ግዙፋዊ ህልዎት የሌለው የንግድ ሥራ ሃብት ወጪ ነው የሚባለው፡-

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፭ (፯) ፊደል ተራ (ሀ) ስር ተራ ቁጥር (፩፣ ፪) ወይም (፫) "ግዙፋዊ ህልዎት የሌለው የንግድ ሀብት" ለሚለው ሀረግ በተሰጠው ትርጉም ከተመለከቱት ግዙፋዊ ህልዎት ከሌላቸው የንግድ ሥራ ሀብቶች ጋር በተያያዘ እነዚህን ሀብቶች ለማግኘት፣ ለመፍጠር፣ ለማሻሻል እና ለማደስ እንዲሁም እነዚህን ሀብቶች ለማግኘት ወይም ለማስተላለፍ የሚወጣ ሌላ ተጓዳኝ ወጪ፣

ለ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፭(፯) ፊደል ተራ (ሀ) ስር ተራ ቁጥር (፬) "ግዙፋዊ ህልዎት የሌለው የንግድ ሥራ ሀብት" ለሚለው ሀረግ በተሰጠው ትርጉም ውስጥ ከተመለከተው ግዙፋዊ ህልዎት የሌለው የንግድ ሥራ ሀብት ጋር በተያያዘ የወጣ ወጪ ነው፡፡

3. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፰ (፪) በተደነገጉት ሁኔታዎች መሠረት በስጦታ የሚገኝ ሀብት ወጪ ንብረቱ በስጦታ በተገኘበት ጊዜ የነበረው ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ነው፡፡

4. የአንድ ንብረት ዋጋ በዚህ አዋጅ ተቀናሽ እንዲደረግ የተፈቀደውን ማንኛውንም ወጪ

b) in relation to a business intangible referred to in paragraph (4) of the definition of "business intangible" in sub article 7 (a) of Article 25 of this Proclamation, the amount of the expenditure.

3. The cost of an asset acquired by way of gift in the circumstances specified in Article 68 (2) of this Proclamation shall be the fair market value of the asset at the time of the acquisition.

4. The cost of an asset shall not include any amount allowed as a deduction under this Proclamation.

5. The cost of an asset of a person shall include any amount given by the person for the grant of an option to acquire the asset.

6. The cost of an asset of a person shall not be reduced by an impairment write down in relation to the asset made in the financial accounts of the person.

7. If a person disposes of a part of an asset, the cost of the asset shall be apportioned between the part of the asset retained and the part disposed of in accordance with their respective fair market values determined at the time

አይጨምርም፡፡

5. የአንድ ንብረት ዋጋ የንብረቱ ባለቤት ንብረቱን የማግኘት ምርጫ እንዲኖረው ከማድረግ ጋር በተያያዘ የወጡ ወጪዎችን ይጨምራል፡፡
6. የአንድ ንብረት ዋጋ በንብረቱ ላይ በደረሰ ጉዳት ምክንያት በንብረቱ ባለቤት የሂሳብ መዝገብ ላይ ተመዝግቦ የሚገኘውን ተቀናሽ ሂሳብ አያካትትም፡፡
7. አንድ ሰው ከአንድ ሀብት ውስጥ ከፊሉን የሸጠ ወይም የለወጠ እንደሆነ፣ ይህ ሀብት ሲገዛ የነበረውን ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ታሳቢ በማድረግ የሀብቱ ዋጋ በተሸጠው እና በባለሀብቱ እጅ ባለው ድርሻ መካከል ይከፋፈላል፡፡
8. በዚህ አዋጅ መሠረት በግብር ከፋዩ ገቢ ውስጥ የሚካተተው የገንዘብ መጠን እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የአንድ ግብር ከፋይ ሀብት ዋጋ ግብር ከፋዩ ሀብቱን ሲያገኝ የተቀበለውን ወይም ሊቀበለው የሚችለውን ማንኛውንም ድጎማ፣ ተመላሽ፣ ኮሚሽን ወይም ሌላ ማንኛውንም የገንዘብ ድጋፍ አይጨምርም፡፡
9. የመስተዳደር ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ የአንድን ንብረት ዋጋ ለመወሰን ከግምት ውስጥ ሊገቡ የሚገባ ሌሎች ዝርዝር ድንጋጌዎችን ሊወስን ይችላል፡፡

### ፷፯ የንግድ ሀብት የተጣራ የመዝገብ ዋጋ

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የአንድ የንግድ ሀብት

the person acquired the asset.

8. The cost of an asset of a person shall not include the amount of any grant, subsidy, rebate, commission, or other financial assistance received or receivable by a person in respect of the acquisition of the asset, except to the extent to which the amount is included in the business income of the person taxable under this Proclamation.
9. The Executive Council may determine others detail provisions, taking into consideration, for determining the cost of assets by the Regulation to be issued.

### 67. Net Book Value of a Business Asset

1. Subject to sub-article (2) of this Article, the net book value of a business asset of a taxpayer is the cost of the asset reduced by any deductions allowed to the taxpayer in respect of the asset under Article 25(1) of this Proclamation, or that would have been allowed but for Article 25(3) of this Proclamation.

2. If Article 66 (7) of this Proclamation applies to a business asset of a taxpayer, the net book value of the asset is the cost apportioned to the asset under the same Article reduced by any deductions allowed to the taxpayer in respect of the asset under Article 25(1) of this Proclamation, or that would

የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ነው የሚባለው ሀብቱን ለማግኘት ከወጣው ወጪ ላይከሀብቱ ጋር በተያያዘ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፭(፩) መሠረት የተፈቀደው ተቀናሽ ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፭(፫) ተግባራዊ ባይደረግ ኖሮ የሚፈቀደው ተቀናሽ ከተቀነሰ በኋላ የሚገኘው ውጤት ነው፡፡

2. የአንድ ግብር ከፋይ የንግድ ሀብት የተጣራ የመዝገብ ዋጋ በሚሰላበት ጊዜ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፮(፯) ተፈፃሚ የሚደረግ ከሆነ የንግድ ሥራ ሀብቱ የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ነው የሚባለው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፮(፯) መሠረት የሀብቱ ድርሻ ነው ተብሎ ከሚወሰደው ወጪ ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፭(፩) ለግብር ከፋዩ የሚደረገው የወጪ ተቀናሽ ወይም የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፭(፬) ድንጋጌ ተግባራዊ ባይደረግ ኖሮ ተቀናሽ ይደረግ የነበረው ወጪ ከተቀነሰ በኋላ የሚቀረው ሂሣብ ነው፡፡

**፷፰ ሀብትን በማስተላለፍ የሚገኝ ገቢ**

1. አንድ ሰው አንድን ሀብት ሲያስተላልፍ ከዚህ ሀብት የተገኘ ገቢ ሆኖ የሚወሰደው ሀብቱን ሲያስተላልፍ የተቀበለው ወይም የሚቀበለው ጠቅላላ የገንዘብ መጠን ሲሆን፣ ሀብቱ በተላለፈበት ጊዜ በዓይነት የተገኘውን ማንኛውንም ጥቅም ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ይጨምራል፡፡
2. ለኢትዮጵያ በጎ አድርጎት ድርጅት ወይም ለኢትዮጵያ ማህበር የሚሰጥን እርዳታ ሳይጨምር ሀብት በስጦታ የተላለፈ እንደሆነ ሀብቱ በተላለፈበት ጊዜ ያለው የሀብቱ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ከሀብቱ የተገኘ ገቢ

have been allowed but for Article 25(4) of this Proclamation, that relate to the cost apportioned to the asset under Article 66 (7) of this Proclamation.

**68. Income Acquisition for the Disposal of an Asset**

1. The consideration for the disposal of an asset by a person is the total amount received or receivable by the person for the asset, including the fair market value of any consideration-in-kind determined at the time of disposal.
2. If an asset is disposed of by way of gift, other than as a donation to an Ethiopian Charity or Ethiopian Association, the consideration for the disposal shall be the fair market value of the asset at the time of the disposal.
3. The consideration for the disposal of an asset by a person includes the consideration for the grant of an option in relation to the disposal of the asset, but only if the person has not been subject to tax in respect of any gain made on the grant of the option.
4. If an asset has been lost or destroyed by a person, the consideration for the asset includes any compensation, indemnity, or damages received or

እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

3. አንድ ሰው ሀብቱን በማስተላለፍ ያገኘው ገቢ፣ ሀብቱን ከማስተላለፍ ጋር በተያያዘ ከቀረበለት ምርጫ ያገኘውን ጥቅም ይጨምራል፡፡ ሆኖም ይህ ጥቅም እንደ ገቢ ተደርጎ የሚወሰደው ከቀረበለት ምርጫ ጋር በተያያዘ ባገኘው ጥቅም ላይ ግብር ያልከፈለ ሲሆን ብቻ ነው፡፡

4. አንድ ሀብት የጠፋ ወይም የወደመ እንደሆነ፣ የዚህ ሀብት ዋጋነው የሚባለው ባለሀብቱ ሀብቱ በመጥፋቱ ወይም በመውደሙ ምክንያት የተቀበለው ወይም የሚቀበለው የካሳ መጠን ሲሆን የሚከተሉትን ይጨምራል፡፡

   ሀ/ በመድን ፖሊሲ መሠረት፣ በካሳ ወይም በሌላ ስምምነት ምክንያት የተቀበለውን ወይም የሚቀበለውን የገንዘብ መጠን፣

   ለ/ በድርድር ምክንያት የሚቀበለውን የገንዘብ መጠን፣ ወይም

   ሐ/ የፍርድ ቤት ውሳኔን ተከትሎ የተቀበለውን ወይም የሚቀበለውን የገንዘብ መጠን፣

5. አንድ ሰው በአንድ ግብይት ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሀብቶችን ያስተላለፈ እንደሆነና የእያንዳንዱ ሀብት ዋጋ ተለይቶ ያልታወቀ እንደሆነ፣ ሀብቶቹ በተላለፈበት ጊዜ ባለው ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መሠረት በማስተላለፉ ምክንያት የተገኘው የገንዘብ መጠን ለተላለፉት ሀብቶች እንደየድርሻቸው ይደለደላል፡፡

6. አንድ ግብር ከፋይ የተላለፈውን ሀብት ዋጋ

receivable by the person as a result of the loss or destruction, including amounts received or receivable:

   a) under an insurance policy, indemnity, or other agreement;

   b) under a settlement; or

   c) as a consequence of a judicial decision.

5. If two or more assets are disposed of by a person in a single transaction and the consideration for each asset is not specified, the total consideration shall be apportioned among the assets disposed of in proportion to their respective fair market values determined at the time of the disposal.

6. If a taxpayer is unable to provide documentary evidence of the consideration for the disposal of an asset, the consideration shall be the fair market value of the asset at the time of disposal.

**69. Deferral of Recognition of Gain or Loss**

1. For the purposes of this Proclamation and subject to sub-article (2) of this Article, no gain or loss shall be taken to arise on the disposal of an asset:

የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ ያልቻለ እንደሆነ ሀብቱ በተላለፈበት ጊዜ የነበረው ትክክለኛ የገበያ ዋጋ የሀብቱ ዋጋ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

**፷፱. ጥቅምን ወይም ኪሳራን ስለ ማስተላለፍ**

1. ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል፣ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በሚከተሉት ሁኔታዎች ምክንያት አንድ ሀብት ሲሸጥ ወይም ሲለወጥ የተገኘ ማናቸውም ዓይነት ጥቅም ወይም የደረሰ ኪሳራ ለግብር አከፋፈል ከግምት ውስጥ አይገባም፡፡

   ሀ/ ባልና ሚስት በሚፋቱበት ጊዜ የሚደረግ የንብረት ክፍፍል፣

   ለ/ አንድ ሰው በመሞቱ ምክንያት ለውርስ አጣሪው ወይም ለወራሹ ሀብት ሲተላለፍ፣

   ሐ/ ሀብቱ በመጥፋቱ ወይም በመውደሙ ወይም ሀብቱ ለህዝብ ጥቅም ሲባል በመንግሥት በመወሰዱ ምክንያት (ከዚህ በኋላ "የተተካው ንብረት” ተብሎ የሚጠቀስ) የተገኘው ገቢ ገንዘቡን በተቀበለው ሰው አማካኝነት ሀብቱ በጠፋ ወይም በወደመ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ወይም ቢሮው በሚፈቅደው ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ ተመሳሳይ ሀብት (ከዚህ በኋላ "የመተኪያ ሀብት” ተብሎ የሚጠቀስ) ለማፍራት የዋለ እንደሆነ ወይም፣

   መ/ ሀብቱ (ከዚህ በኋላ "የተተካው ሀብት " ተብሎ የሚጠራ) ዋጋው የሚቀንስ ሀብት የሆነ እንደሆነና ባለሀብቱ የተተካው

a) between spouses as part of a divorce settlement;

b) by reason of the transmission of the asset on the death of a person to an executor or successor;

c) by reason of the loss or destruction, or compulsory acquisition of the asset (referred to as the “replaced asset”) if the consideration for the disposal is reinvested by the recipient in an asset of a like kind (referred to as a “replacement asset”) within one year of the disposal or within such further period as the Bureau shall allow; or

d) if the asset is a depreciable asset (referred to as the “replaced asset”) and the person acquires a depreciable asset of a like kind to be wholly used to derive amounts included in business income (referred to as the “replacement asset”) within six months after the disposal or within such further period as the Bureau allows.

2. Sub-article (1)(a) or (b) of this Article shall not apply if the person acquiring the asset will not be subject to tax under

ሀብት በጠፋ ወይም በወደመ በስድስት ወር ጊዜ ወይም ቢሮው በሚፈቅደው ከዚህ የረዘመ ጊዜ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የንግድ ሥራ ገቢ ለማግኘት የሚውል ዋጋው የሚቀንስ (ከዚህ በኋላ "የመተኪያ ሀብት " ተብሎ የሚጠራ) ተመሳሳይ ሀብት ያፈራ እንደሆነ፣

